በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE
የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/

ቁጥር: ስ/አ/ጽ/ቤት 165/06

ቀን: 08/03/06 ዓ.ም

ለ፡ ም/ስራ አስኪያጅ /ኦፕሬሽን ዘርፍ/
ም/ስራ አስኪያጅ /ኮርፖሬት ዘርፍ/
ሁሉም የሥራ ሂደቶች
ልዩነት አጣሪ ቡድን
ዋጋ ትመና ቡድን
ሕግ ተገዢ የስጋት ስራ አመራር ቡድን
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

ከ፡ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

የኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ በደብዳቤ ቁጥር 3.0/396/14 በቀን ህዳር 04/2006 ዓ.ም. ባለሥልጣኑ እና አስፈፃሚ የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ በመሆን በጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የሚሰጥበት አሠራር ሠነድ መዘጋጀቱን፣ ወደፊትም ከየአስፈፃሚ መ/ቤቶች በመምረጫ መስፈርቱ መሠረት በፕሮግራሙ የሚካተቱ ድርጅቶችን ዝርዝር ሲልኩ እንደሚያሳውቅ እና ለተጠቃሚዎቹ አስፈላጊውን የተፋጠነ አገልግሎት እንዲሰጣቸው ገልፆ ጽፎልናል፡፡

በመሆኑም ለክትትልና አፈፃፀም ይረዳችሁ ዘንድ የአሠራር ሰርኩላሩን ኮፒ ከዚህ ሸኚ ጋር የተላከ መሆኑን እገልፃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

Ethiopian Revenues and Customs Authority

ቁጥር 3-0/346/14
Ref No.
ቀን
Date

ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
ለሞጆ ደረቅ ወደብ ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
<u>በያሉበት፣</u>

ጉዳዩ፦ <u>የፀደቀ የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት የሚሰጥበት አሠራር ሰነድ መላክን ይመለከታል፣</u>

ባለስልጣኑ እና አስፈፃሚ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በጋራ በመሆን በጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሰርፍኬት የሚሰጥበት አሠራር ሰነድ ተዘጋጅቷል።

ስለሆኑም ወደፊት ከየአስፈፃሚ መ/ቤቶች በመምረጫ መስፈርቱ መሠረት በፕሮግራሙ የሚካተቱ ድርጅቶችን ዝርዝር ሲልኩልን የምናሳውቃችሁ ሲሆን ለተጠቃሚዎቹ አስፈላጊውን የተፋጠነ አገልግሎት እንዲሰጣቸው እንዲደረግ እያሳሰብን የህግ ማስከበር ዘርፍም ከቅ/ጽ/ቤቶቹ ጋር በመተባበር የተቀናጀ የኢንተለጀንስ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግ በዚህ ደብዳቤ ግልባጭ እንዲያውቀው ተደርጓል።

"ከሠላምታ ጋር"

ይዳኪ ግዛኸኝ
ዋና ዳይሬክተር
ፕሮግራም ዲዛይንና
ሥራዎች ዘርፍ

<u>ግልባጭ፣</u>
- ለዋና ዳይሬክተር
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ሥንዎች ዘርፍ
- ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ... ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አዲት አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣</u>

አዲስ አበባ ቃሊቲ ...
A.A Kality Customs ...
የሰነድ ሥራ አመራር ክፍል
የደረሰበት ቀን 25/03/06
የተቀባዩ ስም
ፊርማ
የተመራበት ሥራ ሂደት/ክፍል
የገቢ ሰነድ ቁጥር
የተመለሰበት ቀን
መለያ ቁጥር

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

## የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት የሚሰጥበት አሠራር

ህዳር 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ፡

ማውጫ

1.መግቢያ ........ 1

2.ዓላማ ........ 2

3.ቀላል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ተጠቃሚዎችን የመምረጫ መስፈርትና የዕውቅና ሠርተፍኬት አሰጣጥ ሂደት፣ ........ 2

3.1ቀላል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠቃሚዎች መምረጫ መስፈርት ........ 2

3.1.1አምራች ........ 3

3.1.2ላኪ ........ 3

3.1.3. በኢንዱስትሪ ልማት ለተሰማሩ ........ 5

3.1.4 የግብርና ምርትን በማዘጋጀት ለወጪ ገበያ በመላክ ለተሰማሩ ........ 19

3.1.5 በማዕድን ማምረት እና ወደ ውጪ መላክ ለተሰማሩ ........ 37

3.2. ቀላል የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ተጠቃሚነት ሰርተፍኬት የሚሰጥበት የሥራ ሂደት ........ 39

3.2.1.ቀላል የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ተጠቃሚነት ሰርተፍኬት የሚሰጥበት ስርዓት ስዕላዊ መግለጫ፣ ........ 39

3.2.2.ቀላል የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ተጠቃሚነት ሰርተፍኬት የሚሰጥበት ዝርዝር መግለጫ ........ 40

4.የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬትይዘት ........ 42

5.የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚያስገኘው ጠቀሜታ እና የሚያስከትለው ግዴታ ........ 43

5.1የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚያስገኘው ጠቀሜታ ........ 43

5.2.ዕውቅና ሠርተፍኬት የተሰጠው የሚኖርበት ግዴታ ........ 44

6. የአስፈፃሚ መ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ........ 45

6.1.የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚሰጡ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ........ 45

6.2.የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት ........ 46

## 1.መግቢያ

መንግስት ሀገሪቷ ካለችበት ድህነት ውስጥ በአጭር ጊዜ በማውጣት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ እየወሰዳቸው ካሉ እርምጃዎች መካከል አንዱ የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ነው፡፡

ይህን የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከማሳካት አንፃር ከፍተኛ ሚና የሚኖራቸውን በተለያዩ ዘርፍ የተሰማሩ ወይም በቀጣይ የሚሰማሩ ልማታዊ ባለሀብቶችን መንግስት በልዩ ሁኔታ የሚደገፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጉምሩክ አሠራርን ለማሻሻል በቅርቡ በአደረገው ጥናት ልዩ ትኩረት ከሰጠው ጉዳይ ዋነኛው ለልማታዊ ባለሀብቱ በተለይ ለአምራችና ላኪዎች በተለየ ሁኔታ የተቀላጠፈ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሥርዓት መቅረፅና መዘርጋት ነው፡፡

በዚህ የአሠራር ማሻሻያ ጥናት አምራችና ላኪዎችን ጨምሮ ሌሎች ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ጉልህ ድርሻ ለሚኖራቸው የኢንቨትመንትና ፕሮጀክቶች በልዩ ሁኔታ የተቀላጠፈ የጉምሩክ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ በመቅረፅ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል፡፡ በልዩ ሁኔታ የተቀላጠፈ የጉምሩክ አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸው ልማታዊ ባለሀብት የመምረጥና ዕውቅና የመስጠት ተግባር በሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ቢሆን አግባብነት ያላቸውን ልማታዊ ባለሀብት ከመደገፍ አኳያ ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆን ታምኖበታል፡፡

በዚህ መሠረት በልዩ ሁኔታ የተቀላጠፈ የጉምሩክ አገልግሎት ሊያገኙ የሚገባቸውን ልማታዊ ባለሀብቶችን በሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች የመምረጡና ዕውቅና የመስጠቱ ሂደት ግልፅ፣ ወጥ፣ ለአፈፃፀም ቀላልና ኃላፊነትና ተጠያቂነት ባለበት መልኩ መወጣት የሚቻልበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በመሆኑም በዚ ህ ሰነድ የሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች በልዩ ሁኔታ የጉምሩክ አገልግሎት ሊያገኙ የሚገባቸውን ልማታዊ ባለሀብቶች የሚመርጡበት ግልፅ የሆነ መስፈርት፣ የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚሰጥበት ሂደት፣ መረጃዎችን በአስፈፃሚ መ/ቤቶች እና

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መካከል የሚለዋወጡበትን መንገድ፣ በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለሀብቶች የሚያገኙትን ጥቅም እንዲሁም የአስፈፃሚ መ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር ተለይቷል።

ይህን መነሻ በማድረግ የሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ከየራሳቸው ህጐችና ዓላማዎች ጋር በማጣጣም የየራሳቸው ግልፅ የአፈፃፀም መመሪያና ማንዋል የሚያወጡ ይሆናል።

## 2.ዓላማ

የዚህ ሰነድ ዓላማ ልማታዊ ባለሀብቶችን የሚመለከታቸውን የመንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ግልፅ እና ወጥ በሆነ መልኩ ለመምረጥ የሚችሉበት እና ለተመረጡት ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት የሚያገኙበትን የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲሁም ከዚህ ጋር በተያያዘ በአስፈፃሚ መ/ቤቶች እና በባለስልጣኑ መ/ቤት መካከል ሊኖር የሚገባውን የመረጃ ልውውጥ ማመላከት ነው።

## 3.ቀላል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ተጠቃሚዎችን የመምረጫ መስፈርትና የዕውቅና ሠርተፍኬት አሰጣጥ ሂደት፣

## 3.1ቀላል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠቃሚዎች መምረጫ መስፈርት

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ላይ ለዕቅዱ መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው ተብለው የተለዩ የኢንዱስትሪ ዘርፍ እና ምርቶችን ለውጪ ገበያ የሚያቀርቡ ቀላል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ይሆናሉ። ይሁን እንጂ በሌሎች ዘርፎችም የተሰማሩ ቢሆንም ተጨማሪ እሴት የሚፈጥሩ እስከሆኑ ድረስ በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

በዚሁ መሠረት ቀላል የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑ ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጉልህ ድርሻ የሚኖራቸው ልማታዊ ባለሀብቶችን ለመምረጥ የሚያስችል የየዘርፉን ባህሪ ታሳቢ ያደረገ ግልፅ የመምረጫ መስፈርት ማዘጋጀት ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ ፍትሃዊነትን ያሰፍናል። እንዲሁም ለአፈፃፀም ቀላል ይሆናል። ከዚህ አንፃር በዚህ ሰነድ ለመነሻነት ለአምራቾች እና ላኪዎች በመምረጫ መስፈርት ውስጥ ሊካተቱ የሚገቡ ነጥቦችን እንደሚከተለው ለመዘርዘር የተሞከረ ሲሆን፣ የሌሎችም ዘርፎች

በተመሳሳይ መልኩ የየዘርፉን ባህሪ ታሳቢ በአደረገ መልኩ በቀጣይ በአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚቀረጽ ይሆናል፡፡

### 3.1.1አምራች

በዚህ ሰነድ አምራች ሲባል በኢንዱስትሪ ዘርፍም ሆነ በግብርና ዘርፍ የተሰማሩትን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፣ በግብርና ዘርፍ ለተሰማሩት የግብርና ሚኒስቴር እንዲሁም በማዕድን ዘርፍ ለተሰማሩ የማዕድን ሚኒስቴር በዚህ ሰነድ በየዘርፉ በተዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት መሠረት ልማታዊ ባለሀብቶች በመምረጥ የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን የዕውቅና ሠርተፍኬት እንዲሰጣቸዉ ለባለሥልጣኑ የሚያሳውቁ ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት የመምረጫ መስፈርቱ ውጥ እና ግልፅ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር በአምራችነት የተሰማሩ ልማታዊ ባለሀብቶች የሚመረጡበት መስፈርት የሚከተሉትን ነጥቦች የሚያካትት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

- በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ቅድማያ ትኩረት የተሰጠው
- የሚፈልገው የተጨማሪ እሴት መጠን
- የፈጠረው የስራ ዕድል
- የኢንቨስትመንት ወጪ መጠን
- የምርት አቅም (Production Capacity)
- የውስጥ አሰራርና ቁጥጥር ስርዓት
- ምርቱን ወደ ውጪ የሚልክ
- ገቢ ዕቃን የሚተካ ዕቃ የሚያመርት
- በምርት ሂደት የጊላና የፊት ትስስር መፍጠር (Background & forward)
- ከፍተኛ የሀገር ውስጥ ታክስ የሚከፍል ወይም የመክፈል አቅም ያለው
- የተደራጀና በአውቶሜሽን ስርዓት የታገዘ የመረጃ ስርአት ያለው

### 3.1.2ላኪ

በዚህ ሰነድ ላኪ ሲባል፤ እራሱ አምርቶ የሚልክም ሆነ፣ በሌሎች የተመረቱትን ተረክቦ የሚልክን እንደሚያካትት ታሳቢ የተደረገ ሲሆን፣ እራሱ አምርቶ ለሚልከው ቀደም ሲል በክፍል 3.1.1. ላይ እንደተገለፀው የመምረጡ ስራ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና በግብርና ሚኒስቴር የሚከናወን ሲሆን ከአምራቾች ተረክበው የሚልኩ ልማታዊ ባለሀብቶችን የመምረጡ

ተግባር ደግሞ በንግድ ሚኒስቴር የሚከናውን ይሆናል። በዚሁ መሠረት በላኪነት የተሰማሩ ልማታዊ ባለሀብቶችን ወጥ በሆነ መልኩ ለመምረጥ እንዲቻል የሚከተሉት ነጥቦች የመምረጫ መሥፈርት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል።

- ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ
- በወጪ ዕቃ ገበያ አዲስ ምርት ወይም ዕቃ ለውጪ ገበያ የሚያቀርብ
- በወጪ ዕቃ ገበያ አዲስ የገበያ መዳረሻ መፍጠር
- የኢንቨስትመንት ወጪ መጠን
- የፈጠረው የስራ ዕድል
- የውስጥ አሰራርና ቁጥጥር ስርዓት
- የተደራጀና በአውቶሜሽን ስርዓት የታገዘ የመረጃ ስርዓት ያለው
- ከፍተኛ የሀገር ውስጥ ታክስ የሚከፍል ወይም የመክፈል አቅም ያለው
- በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምርቶችን ወደ ውጭ የሚልክ

## በዘርፍ ተለይቶ የተዘጋጀ መምረጫ መስፈርት

ከላይ በክፍል 3.1.1. እና 3.1.2 የተገለፀውን በመነሻነት የተዘጋጀውን የመምረጫ መስፈርት መሠረት በማድረግ፤ የየዘርፉን ባህሪ ከግንዛቤ በማስገባት የሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ዝርዝር መስፈርት እንዲያዘጋጁ በማድረግ በዚህ ሰነድ እንዲካተት ተደርጓል። በተዘጋጀው ዝርዝር መስፈርት ውስጥም ባለሀብቱ ሊያሟላው የሚገባው መለኪያ በግልፅ እንዲጠቀስ የተደረገ ሲሆን ለምሳሌ የኢንቨስትመንት የካፒታል ወጪ መጠን እንደ አንድ መስፈርት የተወሰደ ከሆነ የኢንቨስትመንት የካፒታል ወጪው መጠን ከምን ያህል በላይ ሲሆን መስፈርቱን እንደሚያሟላ በግልፅ ተቀምጧል።

ከዚህ በተጨማሪም በተዘጋጀው የመምረጫ ስርዓት ውስጥ አንድ ባለሀብት ከተቀመጡት ዝርዝር መምረጫ መስፈርት ውስጥ ምን ያህሉን ሲያሟላ ሊመረጥ እንደሚችል በየዘርፍ ተለይቶ ተገልጿል። በዚህ ሰነድ በየዘርፉ ተለይቶ የተዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት ለመነሻ እንዲሆን ታሳቢ የተደረገ ሲሆን የመቅረጫ መስፈርቱ በየጊዜው እየታየ ሊከለስ ይችላል። ቀደም ሲል በክፍል 3.1.1. እና 3.1.2. ላይ በተጠቀሰው የመምረጫ መስፈርት መሠረት በሚመለከታቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች የተዘጋጀው ዝርዝር መስፈርት በየዘርፍ ተለይቶ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.1.3. በኢንዱስትሪ ልማት ለተሰማሩ

በዚህ ዘርፍ የተሰማሩትን ልማታዊ ባለሀብት የመምረጥ ኃላፊነት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲሆን በሚኒስተር መ/ቤቱ የዘጋጀው የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባቸዉን ልማታዊ ባለሀብቶች ለመምረጥ የሚያስችለው ዝርዝር የመምረጫ መስፈርት በየተሰማሩበት የማምረቻ ዘርፍ በመለየት ማለትም በቆዳ፣ በኢንዱስትሪ፣በጨርቃ ጨርቅ፣በአግሮ ፕሮሰስ ኢንዱስትሪ፣ በብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ለተሰማሩት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### ሀ) በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት

በቆዳና የቆዳ ኢንቨስትመንት ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሀብቶች እያካሄዱ ያሉት ልማት አጠናክረው እንዲሄዱና በገበያ ተወዳዳሪ ምርት በማምረት አገሪቱ ለተያያዘችው የአምስት አመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሳካት አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ደረጃ በመለየት እንዲበረታቱና እንዲጠናከሩ የኤክስፖርት ዝግጁነታቸውን በመገምገም ፈጣን የጉምሩክ ሥነ ስርአት ተጠቃሚ ማድረግ እና ሌሎችንም የማበረታቻ ድጋፎች መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኤክስፖርት ልማቱ ውስጥ የሚደያርጉትን ተሳትፎና ውጤታማነት በመገምገም በዚህ የማበረታቻ ስርአት መጠቀም እንዲችሉ የሚያስችል የሚከተለው የመምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቷል፡፡

## በኤክስፖርት ለተሰማሩ የቆዳና ቆዳ ዉጤት አምራቾች የቀላል የጉምሩክ ስነ ስርዓት ተጠቃሚነት መምረጫ መስፈርት

| ተ/ቁ | የመምረጫ መስፈርት | የሚይዘው ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | ደረጃ | ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.1 | ቆዳ ፋብሪካዎች | | | | | |
| 1 | በአመታዊ የኤክስፖርት ዕቅድ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው | 20% | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ10 ሚሊዮን ዶላር በላይ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ5-10 ሚሊዮን ዶላር | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ2-5 ሚሊዮን ዶላር | መካከለኛ | 2 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ2 ሚሊዮን ዶላር በታች | ዝቅተኛ | 1 | |
| 2 | ወቅታዊ የኤክስፖርት አፈፃፀም ከአቅዱ አንፃር | 40% | የኤክስፖርት አፈፃፀሙ በየወሩ በአማካይ ከ500 ሺ.ህ ዶላር በላይ የሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | የኤክስፖርት አፈፃፀሙ በየወሩ በአማካይ ከ200- 500 ሺ.ህ ዶላር የሆነ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ50-200 ሺ.ህ ዶላር የሆነ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | -የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ50 ሺ.ህ ዶላር በታች | ዝቅተኛ | 1 | |
| 3 | ለቆዳ ውጤት አምራቾች /በተለይ ለጫማ አምራቾች/ ያለቀለት ቆዳ አቅርቦት ማመቻቸት | 10% | ከፍተኛ ኤክስፖርተር ለሆኑ የጫማ ፋብሪካዎች ያለቀለት ቆዳ ያቀበለ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | መካከለኛ ኤክስፖርተር ለሆኑ ያቀበለ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | ዝቅተኛ ኤክስፖርተር ለሆኑ አምራቾች ያቀበለ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | ለአገር ውስጥ አምራቾች ብቻ ያለቀለት ምርቱን ያቀበለ | ዝቅተኛ | 1 | |
| 4 | የአካባቢ ጥበቃ ዝግጁነት | 10% | ፕራይመሪ እና ሰከንደሪ ትሪትመንት ፕላንት ያለው | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | ፕራይመሪ ትሪትመንት ፕላንት ኖሮት ሁለተኛውን እያዘጋጀ ያለ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | ፕራይመሪ ትሪትመንት ፕላንት ብቻ ያለው | መካከለኛ | 2 | |
| | | | ትሪትመንት ፕላንት የሌለዉ | ዝቅተኛ | 1 | |

| ተ/ቁ | የመምረጫ መስፈርት | የሚይዘው ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | ደረጃ | ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ድርጅቱ ለሰራተኛ የፈጠረው የስራ እድል | 20% | ከ500 ሰራተኛ በላይ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | -ከ 300 - 500ሰራተኞች የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | ከ150 - 299 ለሚሆን ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | -ከ150 በታች ለሆነ ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 | |
| 1.2 | **የጫማ ፋብሪካዎችን** | | | | | |
| 1 | በአመታዊ የኤክስፖርት ዕቅድ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው | 30% | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ4 ሚሊዮን ዶላር በላይ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ2-4 ሚሊዮን ዶላር | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ500ሺ --2 ሚሊዮን ዶላር | መካከለኛ | 2 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ500ሺ ዶላር በታች | ዝቅተኛ | 1 | |
| 2 | ወቅታዊ የኤክስፖርት አፈፃፀም ከእቅዱ አንፃር | 40% | የኤክስፖርት አፈፃፀሙ በየወሩ በአማካይ ከ200 ሺ.ህ ዶላር በላይ የሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | የኤክስፖርት አፈፃፀሙ በየወሩ በአማካይ 100-200 ሺ.ህ ዶላር የሆነ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ50-100 ሺ.ህ ዶላር የሆነ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ50 ሺ.ህ ዶላር በታች | ዝቅተኛ | 1 | |
| 3 | የአቅም አጠቃቀም | 10% | -የአቅም አጠቃቀሙ ከ70% በላይ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | - ›› ›› ከ60-70% ከሆነ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | - ›› ›› ከ50 -59% ከሆነ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | - ›› ›› ከ50% በታች ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 | |
| 4 | ድርጅቱ ለሰራተኛ የፈጠረው የስራ እድል | 20% | ለ200 ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | ከ100 — 199 ሰራተኞች የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | ከ50 እስከ 99 ለሚሆን ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | -ከ50 በታች ለሆነ ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 | |

| ተ/ቁ | የመምረጫ መስፈርት | የሚይዘው ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | ደረጃ | ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.3 | የቆዳ ጓንት፣አልባሳትና ዕቃዎች | | | | | |
| 1 | በአመታዊ የኤክስፖርት ዕቅድ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው | 30% | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ500 ሺ. ዶላር በላይ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ200-500 ሺ.ህ ዶላር | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ100–199 ሺ.ህ ዶላር በላይ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | የኤክስፖርት ዕቅድ ከ100 ሺ.ህ ዶላር በታች | ዝቅተኛ | 1 | |
| 2 | ወቅታዊ የኤክስፖርት አፈፃፀም ከእቅዱ አንፃር | 40% | -የኤክስፖርት አፈፃፀሙ በየወሩ በአማካይ ከ300 ሺ.ህ ዶላር በላይ የሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | - የኤክስፖርት አፈፃፀሙ በየወሩ በአማካይ 50 - 299 ሺ.ህ ዶላር የሆነ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | - የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ30 - 49 ሺ.ህ ዶላር የሆነ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | -የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ30 ሺ.ህ ዶላር በታች | ዝቅተኛ | 1 | |
| 3 | ድርጅቱ ለሰራተኛ የፈጠረው የስራ እድል | 30% | -ለ200 ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 | |
| | | | -ከ100 — 199 ሰራተኞች የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ከፍተኛ | 3 | |
| | | | -ከ50 እስከ 99 ለሚሆን ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | መካከለኛ | 2 | |
| | | | -ከ50 በታች ለሆነ ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 | |

የቆዳ ፋብሪካዎች ፣ የጫማ ፋብሪካዎች እና የቆዳ እቃዎች እና አልባሣት ከተቀመጡት መስፈርቶች አንፃር አጠቃላይ አፈፃፀማቸው 60 በመቶ በላይ ከሆነ የማበረታቻ ስርአቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በሌሎች መስፈርቶች በዚህ የማበረታቻ ስርአት ውስጥ እንደነ በስቴክስ ጫማ ፋብሪካ በልዩ ሁኔታ በዚህ የማበረታቻ ስርአት የሚካተቱ ይሆናል፡፡

ለ) በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ለተሰማሩ የመምረጫ መስፈርት

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ክትትልና ድጋፍ በሚደረግላቸው አምርቶ ለውጪ ገበያ በመላክ የስራ ሂደት ለተሰማሩ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች ልዩ የጉምሩክ አገልግሎትን ማግኘት እንዲችሉ የተጠቃሚዎች የመምረጫ መስፈርቶች እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

በመሠረታዊነት አምራቾች ለምርጫው ለመቅረብ ማሟላት የሚገባቸው፡-

- በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል መሆን፣
- ምርቱን በቀጥታ ወደ ውጭ የሚልኩ ወይንም ምርቱን/ግብዓት ወደ ውጭ ለሚልኩት የሚያቀርቡ መሆን፣
- በኢንስቲትዩቱ ዓመታዊ የኤክስፖርት ዕቅድ ውስጥ የተካተተ መሆን አለበት፣

ከላይ በጥቅል ለተጠቀሱት መስፈርቶች ለመመዘን በሚያስችል ሁኔታ ዝርዝር የነጥብ አሰጣጥ ለጨርቃጨርቅ፣ ለስፌት ውጤቶች አምራቾች እና ለባህላዊ የሽመና ውጤት አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደሚከተለው የቀረበ ሲሆን፣ አንድ ድርጅት ምርጫውን አሟልቶ የፈጣን አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆነው ቢያንስ ከ60 በመቶ በላይ ነጥብ ሲያዝመዘግብ ነው፡፡

1.ለጨርቃጨርቅ (የተለያዩ ክሮች፣ያልተቀለመና የተቀለመ ጨርቅ) አምራች ኢንዱስትሪዎች

| ተ.ቁ | የመምረጫ መስፈርት | መለያ | የሚይዘው ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | በአፈጻጸም ደረጃ የሚሰጥ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ካለው ጠቅላላ ወቅታዊ የማምረት አቅም አኳያ በቀጥታ/በተዘዋዋሪ መልኩ ለውጭ ገበያ የቀረበው መጠን | በቀረበ ሰነድ | 50% | ከ50% በላይ የሆነ | 50 |
| | | | | ከ30%-50% የሆነ | 40 |
| | | | | ከ20%-30% የሆነ | 30 |
| | | | | ከ10%-20% የሆነ | 20 |
| | | | | ከ10% በታች የሆነ | 10 |
| 2 | የፈጠረው ቋሚ የስራ እድል | በቀረበ ሰነድ | 15% | ከ200ሠራተኞች በላይ ከሆነ | 15 |
| | | | | ከ100-200 ሠራተኞች ከሆነ | 10 |
| | | | | ከ100 ሠራተኞች በታች ከሆነ | 5 |
| 3 | ከገነባው የማምረት አቅም የተጠቀመው መጠን (የማምረት አቅም አጠቃቀም) | በቀረበ ሰነድ | 15% | ከ75% በላይ ከሆነ | 15 |
| | | | | ከ50%-75% ከሆነ | 10 |
| | | | | ከ50% በታች ከሆነ | 5 |
| 4 | አመታዊ የወጪ ንግድ ዕቅድና የድጋፍ ፍላጎት ሰነድ ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ያቀረበ ከሆነ | በቀረበ ሰነድ | 10% | | 10 |
| 5 | የተሟላ የፍሳሽ ማጣሪያን በሥራ ላይ ያዋለ (የአከባቢ ጥበቃ ዝግጁነት) | በቀረበ ሰነድ | 10% | | 10 |

2.ለአልባሳት አምራች ኢንዱስትሪዎች

| ተ.ቁ | የመምረጫ መስፈርት | መለያ | የሚይዘው ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | በአፈጻጸም ደረጃ የሚሰጥ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ካለው ጠቅላላ ወቅታዊ የማምረት አቅም አኳያ በቀጥታ/በተዘዋዋሪ መልክ ለውጭ ገበያ የቀረበዉ የምርት መጠን በዋጋ (ወቅታዊ የኤክስፖርት አፈጻጸም) | በቀረበ ሰነድ | 50% | ከ50% በላይ የሆነ | 50 |
| | | | | ከ30%-50% የሆነ | 40 |
| | | | | ከ20%-30% የሆነ | 30 |
| | | | | ከ10%-20% የሆነ | 20 |
| | | | | ከ10% በታች የሆነ | 10 |
| 2 | የፈጠረው ቋሚ የስራ እድል | በቀረበ ሰነድ | 20% | ከ200ሠራተኞች በላይ ከሆነ | 20 |
| | | | | ከ100-200 ሠራተኞች ከሆነ | 15 |
| | | | | ከ100 ሠራተኞች በታች ከሆነ | 10 |
| 3 | ከገነባዉ የማምረት አቅም የተጠቀመዉ መጠን | በቀረበ ሰነድ | 20% | ከ75% በላይ ከሆነ | 20 |
| | | | | ከ50%-75% ከሆነ | 15 |
| | | | | ከ50% በታች ከሆነ | 10 |
| 4 | አመታዊ የወጪ ንግድ ዕቅድና የድጋፍ ፍላጎት ሰነድ ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ያቀረበ ከሆነ | በቀረበ ሰነድ | 10% | | 10 |

## 3.ለባህላዊ የሽመና ውጤት አምራቾች

| ተ.ቁ | የመምረጫ መስፈርት | መለያ | የሚይዘው ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | በአፈጻጸም ደረጃ የሚሰጥ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ካለው ጠቅላላ ወቅታዊ የማምረት አቅም አኳያ በቀጥታ/በተዘዋዋሪ መልኩ ለውጭ ገበያ የቀረበዉ መጠን በዋጋ (ወቅታዊ የኤክስፖርት አፈጻጸም) | በቀረበ ሰነድ | 50% | ከ50% በላይ የሆነ | 50 |
| | | | | ከ30%-50% የሆነ | 40 |
| | | | | ከ20%-29% የሆነ | 30 |
| | | | | ከ10%-19% የሆነ | 20 |
| | | | | ከ10% በታች የሆነ | 10 |
| 2 | የፈጠረው ቋሚ የስራ እድል | በቀረበ ሰነድ | 20% | ከ200ሠራተኞች በላይ ከሆነ | 20 |
| | | | | ከ100-200 ሠራተኞች ከሆነ | 15 |
| | | | | ከ100 ሠራተኞች በታች ከሆነ | 10 |
| 1. | ከገነባዉ የማምረት አቅም የተጠቀመዉ መጠን | በቀረበ ሰነድ | 20% | ከ75% በላይ ከሆነ | 20 |
| | | | | ከ50%-74% ከሆነ | 15 |
| | | | | ከ50% በታች ከሆነ | 10 |
| 2. | አመታዊ የወጪ ንግድ ዕቅድና የድጋፍ ፍላጎት ሰነድ ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቱ ያቀረበ ከሆነ | በቀረበ ሰነድ | 10% | | 10 |

4.በኢንቨስትመንት ሂደት ላይ ለሚገኙ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች የመምረጫ መስፈርቶች

| ተቁ | የመስፈርቱ ዝርዝር | መለያ | ከመቶ የሚይዘው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ከጠቅላላ የማምረት አቅም ቢያንስ 50% ለኤክስፖርት ስራ ቅድሚያ በመስጠት የሚቋቋም | በቀረበ ሰነድ | 30 |
| 2 | ግልፅነትና ተቀባይነት ያለዉ የቢዝነስ እና የኢንቨስትመንት ፕላን ያለው፣ | በቀረበ ሰነድ | 20 |
| 3 | ሊፈጥር የሚችለዉ ቋሚ የስራ እድል ለጨርቃጨርቅ ከ150 ሰዎች፣ ለስፌት ውጤቶች ከ200 ሰዎች በላይ የሆነ | በቀረበ ሰነድ | 20 |
| 4 | በኢንቨስትመንት ፕላኑ መሰረት እያስመዘገበ ባለው አፈጻጸም | በቀረበ ሰነድ | 30 |

ለ) የኬሚካልና ፣ ኮንስትራክሽን ግብዓት እና ፋርማሴትካል ሕክምና መገልገያ ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ

በኬሚካል እና ፋርማሴዩትካል ኢንዱስትሪዎች ቀጥታ በኤክስፖርት ላይ በተሰማሩትና ከውጭ የሚገባውን ምርት በመተካት ስራ ላይ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ተለይተው የመምረጫ መስፈርቶች እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

1. በኤክስፖርተርነት ለተሰማሩ ድርጅቶች

| ተ/ቁ | የመምረጫ መስፈርት | የተሰጠው ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | ደረጃ | ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወቅታዊ የኤክስፖርት አፈፃፀም ከእቅዱ አንፃር | 50% | -የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ60% በላይ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | - የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ55-59 % | ከፍተኛ | 3 |
| | | | - የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ50-54.9% | መካከለኛ | 2 |
| | | | -የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ50% በታች | ዝቅተኛ | 1 |
| 2 | እቅድ ካለፈው ዓመት የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ሁኔታ | 15% | -የኤክስፖርት እቅዱ ካለፈው የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ሁኔታ ከ50% በላይ ካደገ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | -የኤክስፖርት እቅዱ ካለፈው የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ40-49.9% ካደገ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | -የኤክስፖርት እቅዱ ካለፈው የኤክስፖርት አፈፃፀም ሁኔታ ከ30 እስከ 39.9% ካደገ | መካከለኛ | 2 |
| | | | -የኤክስፖርት እቅዱ ካለፈው የኤክስፖርት አፈፃፀም ሁኔታ 10% ካላደረገ | ዝቅተኛ | 1 |
| 3 | የኤክስፖርት መጠን | 25% | የኤክስፖርት መጠኑ በዓመት ከ 3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዳላር በላይ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | የኤክስፖርት መጠኑ በዓመት ከ2-3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | የኤክስፖርት መጠኑ በዓመት ከ1-2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | የኤክስፖርት መጠኑ በዓመት ከ1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በታች ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |
| 4 | ድርጅቱ ለሰራተኛ የፈጠረው የስራ እድል | 10% | -ከ300 በላይ ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | -ከ200-299 ሰራተኞች የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | 100 እስከ 199 ለሚሆን ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | -ከ100 በታች ለሆነ ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |

2. ገቢ ምርቶችን በሚተኩ ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ምርቶችን በማምረት ሥራ ላይ ለተሠማሩ ድርጅቶች

| ተ/ቁ | የመምረጫ መስፈርት | የተሰጠ ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | ደረጃ | ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የምርቱ የትኩረት አቅጣጫ | 40 | -በስትራቴጅክ እቅድ የተያዘ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | -በጥቅል እቅድ የተያዘ ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| 2 | የማምረት አቅም | 10 | በጣም ከፍተኛ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | ከፍተኛ ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | መካከለኛ ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | ዝቅተኛ ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |
| 3 | ለሰራተኛ የፈጠረው ዕድል | 10 | -የተፈጠረው የስራ ዕድል ከ600 በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | -ከ400-600 ›› ›› | ከፍተኛ | 3 |
| | | | -ከ200-400 ›› ›› | መካከለኛ | 2 |
| | | | - ከ200 በታች ›› ›› | ዝቅተኛ | 1 |
| 4 | የአቅም አጠቃቀም | 15 | -የአቅም አጠቃቀሙ ከ70%በላይ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | - ›› ›› ከ60-70% ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | - ›› ›› ከ50 -60% ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | - ›› ›› ከ50% በታች ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |
| 5 | ያስገኘው የእሴት ጭማሪ | 25 | -ከጥሬ እቃው ላይ የጨመረውእሴት 50% ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | - ›› ›› ከ40-50% ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | - ›› ›› ከ30 — 40 ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | - ›› ›› 30% በታች ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |

3. በኤክስፖርት የተሰማሩ የፋርማሲዩቲካል እና የህክምና መሳሪያዎች አምራች ፋብሪካዎች

| ተ/ቁ | የመምረጫ መስፈርት | የተሰጠ ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | ደረጃ | ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወቅታዊ የኤክስፖርት አፈፃፀም ከእቅዱ አንፃር | 25 | -የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ60% በላይ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | - የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ55-59 % | ከፍተኛ | 3 |
| | | | - የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ50-54.9% | መካከለኛ | 2 |
| | | | -የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ50% በታች | ዝቅተኛ | 1 |
| 2 | ወቅታዊ የእቅድ ዕድገት ካለፈው ዓመት የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ሁኔታ | 40 | -የኤክስፖርት እቅዱ ካለፈው የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ሁኔታ ከ50% በላይ ካደገ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | -የኤክስፖርት እቅዱ ካለፈው የኤክስፖርት አፈፃፀሙ ከ40-49.9% ካደገ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | -የኤክስፖርት እቅዱ ካለፈው የኤክስፖርት አፈፃፀም ሁኔታ ከ30 እስከ 39.9% ካደገ | መካከለኛ | 2 |
| | | | -የኤክስፖርት እቅዱ ካለፈው የኤክስፖርት አፈፃፀም ሁኔታ 10% ካላደረገ | ዝቅተኛ | 1 |
| 3 | ወቅታዊ የኤክስፖርት ዕቅድ መጠን | 25 | የኤክስፖርት መጠኑ በዓመት ከ 3 ሚሊዩን የአሜሪካን ዳላር በላይ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | የኤክስፖርት መጠኑ በዓመት ከ2-3 ሚሊዩን የአሜሪካን ዶላር ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | የኤክስፖርት መጠኑ በዓመት ከ1-2 ሚሊዩን የአሜሪካን ዶላር ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | የኤክስፖርት መጠኑ በዓመት ከ1 ሚሊዩን የአሜሪካን ዶላር በታች ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |
| 4 | ድርጅቱ ለሰራተኛ የፈጠረው የስራ እድል | 10 | -ከ300 በላይ ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | -ከ200-299 ሰራተኞች የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | -ከ100 እስከ 199 ለሚሆን ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | -ከ100 በታች ለሆነ ሰራተኛ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |

## ሐ) በአግሮ–ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ በኤክስፖርት ለተሠማሩ ድርጅቶች

| ተራ ቁ. | የመምረጫ መሥፈርት | የተሰጠ ነጥብ ከመቶ | ዝርዝር መሥፈርት | የደረጃ ነጥብ | መግለጫ (ለከፍተኛ፣ ዝቅተኛ ነጥቦች)* |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የ2004 በጀት ዓመት የውጭ ምንዛሬ ገቢ መጠን በዶላር | 45 | 3 ሚሊዮንና በላይ | 4 | ከፍተኛ ነጥብ 45x4= 180 |
| | | | ከ1.5 – 3 ሚሊዮን | 3 | |
| | | | ከ0.5 – 1.5 ሚሊዮን | 2 | ዝቅተኛ ነጥብ 45x1= 45 |
| | | | ከ0.5 ሚሊዮን በታች | 1 | |
| 2 | የ2004 በጀት ዓመት የወጪ ንግድ አፈፃፀም ከዕቅድ አኳያ በመቶኛ | 25 | 85% እና በላይ | 4 | ከፍተኛ ነጥብ 25x4= 100 |
| | | | ከ70% – 84% | 3 | |
| | | | ከ50% – 69% | 2 | ዝቅተኛ ነጥብ 25x1= 25 |
| | | | ከ50% በታች | 1 | |
| 3 | የ2005 በጀት ዓመት የመጀመሪያው አጋማሽ የወጪ ንግድ ገቢ ዕድገት ከ2004 ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በመቶኛ | 30 | ከ35% – 50% | 4 | ከፍተኛ ነጥብ 30x4= 120 |
| | | | ከ20% – 34% | 3 | |
| | | | ከ10% – 19% | 2 | ዝቅተኛ ነጥብ 30x1= 30= 180 |
| | | | ከ10% በታች | 1 | |
| | ድ ም ር | 100 | | | ከፍተኛ ነጥብ →180+100+120= 400 |
| | | | | | ዝቅተኛ ነጥብ → 45+25+30= 100 |

*ለመካከለኛ ነጥቦች በተመሳሳይ ሁኔታ ይሠራል።

መ) በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ሥራ ላይ ለተሠማሩ ድርጅቶች

| ተ/ቁ | የመምረጫ መስፈርት | የተሰጠው ነጥብ | ዝርዝር መስፈርት | ደረጃ | ነጥብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአቅም አጠቃቀም | 30 | -የአቅም አጠቃቀሙ ከ85%በላይ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | - ›› ›› ከ75-85% ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | - ›› ›› ከ60-75% ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | - ›› ›› ከ60% በታች ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |
| 2 | የፈጠረው የስራ ዕድል | 30 | ከ 300 በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | -ከ 101- 300 ›› ›› | ከፍተኛ | 3 |
| | | | -ከ 50 - 100 ›› ›› | መካከለኛ | 2 |
| | | | -ከ 50 በታች ›› ›› | ዝቅተኛ | 1 |
| 3 | ያስገኘው የእሴት ጭማሪ | 20 | ከጥሬ እቃው ላይ የጨመረው እሴት 50%ና በላይ ከሆነ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | ›› ›› ›› ከ36%-50% ከሆነ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | ›› ›› ›› ከ15% — 35% ከሆነ | መካከለኛ | 2 |
| | | | ›› ›› ›› ከ15% በታች ከሆነ | ዝቅተኛ | 1 |
| 4 | ተፈላጊ የመረጃ አቅርቦት | 20 | የተጠየቀውን መረጃ በ 1 ቀን ውስጥ ከአቀረበ | በጣም ከፍተኛ | 4 |
| | | | የተጠየቀውን መረጃ በ 3 ቀናት ውስጥ ከአቀረበ | ከፍተኛ | 3 |
| | | | የተጠየቀውን መረጃ በ 5 ቀናት ውስጥ ከአቀረበ | መካከለኛ | 2 |
| | | | የተጠየቀውን መረጃ በ 7 ቀናት ውስጥ ከአቀረበ | ዝቅተኛ | 1 |

### 3.1.4 የግብርና ምርትን በማዘጋጀት ለወጪ ገበያ በመላክ ለተሰማሩ

የግብርና ምርቶች አዘጋጅቶ ላኪ ሲባል፤ በእራሱ ማሳ አምርቶና አርብቶ/አድልቦ ለኤክስፖርት አዘጋጅቶ የሚልክ የግል ላኪ፣ ህብረት ሥራ ማህበር ወይም ዩኒየን ወይም አቅርቦት ምርት ከአቅራቢዎች፣ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ገዝቶ በራሱ ምርት ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ ወይም ከሌሎች ማዘጋጃና ማከማቻ ኢንዱስትሪ አዘጋጅቶ በሚፈለገው ፓኬጂንግ ተጠቅሞ የሚልከውን ሁሉ ያካትታል።

ሀ. ወደ ወጪ በመላክ የተሰማሩ ልማታዊ ባለሀብቶች የግል ላኪዎች ህብረት

በዚህ ዘርፍ የተሰማሩትን ልማታዊ ባለሀብት የመምረጥ ኃላፊነት የንግድ ሚኒስቴር ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ ከሚያደርግላቸው የግምብርና ምርቶችን ወደ ውጪ በመላክ ከተሰማሩ ባለሀብቶች መካከል ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ሊያገኙ የሚገቡ ልማታዊ ባለሀብቶችን /የግል፣የህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒቶች የሆኑ ላኪዎች ይጨምራል/ ለመምረጥ ያዘጋጀው ዝርዝር መስፈርት እንደሚከተለው ተካቷል።

1. በአለፉት ሶስት ዓመታት ምርት ልከው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ያስገኙ በዚህም መሠረት በየምርት ዓይነቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ረገድ ከ1-10ኛ ደረጃ ያላቸው፤
2. ከአለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ አዳዲስ ምርት በማስተዋወቅ ኤክስፖርት እያደረጉ ያሉ (ቢያንስ ከአንድና ከዚያ በላይ ምርት ዓይነትና ከ10 ኮንቴነር በላይ የላኩ)
3. በነባር ገበያ መዳረሻ የገበያ ድርሻን እያሳደገ የመጣ ላኪ (በየዓመቱ ቢያንስ ከ5 በመቶ በላይ ያሳደገ)
4. ወደ አዳዲስ ገበያዎች ለመግባት የገበያ ማስፋፊያ ሥራ በመስራት ምርት የሸጠ /ምርት ገዢ ያፈራ(ከአንድና ከዚያ በላይ ሀገር ያስገባ)፣
5. በየዓመቱ ምርት አዳዲስ ገዢ ደንኞችን የሳበና የሸጠ ( ቢያንስ ከአንድ በላይ አዲስ ምርት ገዢ ደንበኛ የሳበና ከ10 ኮንቴነር በላይ ምርት የሸጠ)
6. ከሌሎች ተፎካካሪ ላኪዎች በተሻለ ዋጋ ምርት የሸጠ ቢያንስ በአንድ መዳረሻ ገበያ በተመሳሳይ ምርት ዓይነትና ጥራት ደረጃ ከተመዘገበው አማካይ በዓለም ገበያ ዋጋ 15-20 እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣

7. የምርት ማዘጋጃና ማከማቻ፣ የምርት ጥራት ፍተሸ ማሽን፣ ብትን ምርትን በኮንቴነር ማሸጊያ ብሎወር ማሽን ያለው ወይም ይህንን አገልግሎት ለሌሎች በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚሰጥ ወይም የመስጠጥ አቅም ያለው፣

8. የውስጥ አሰራርና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ የምርት ብክነትን፣ በወቅቱ አዘጋጅቶ መላክን፣ በደንበኞች ፍላጎት ላይ ተመሠረተ ጥራት፣ አሰተማማኝ አቅርቦት እንዲኖር ተግቶ የሚሠራ

9. በሕገወጥ ተግባር ያልተሠማራ (ያለምክንያት ዴፎልት ያደረገ፣ የምርት ጥራትን የሚያበላሽ፣ ከዋጋ በታች የሸጠ፣ ያለአግባብ ኤክስፖርት ምርት ያከማቸ መሆን የለበትም)

10.የአጭርና የረጅም ጊዜ የቢዝነስ ዕቅድ/ ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቶ የሚንቀሳቀስ፣

11.የተደራጀ ቢሮና በአውቶሜሽን ስርዓት በታገዘ የመረጃ ስርዓት የሚጠቀም፤

12. ለሰራተኞቹ ፍትሃዊ የሆነ የእድገት፣ ዝውውርና የኢንሴንቲቭ አሰራርን በመዘርጋትና በመተግበር የድርጅቱን ምርታማነት እያሳደገ ያለ ላኪ መሆን አለበት።

ከላይ ለተጠቀሱት መስፈርቶች የተሰጠ ነጥብ

| ተቁ | የመስፈርቱ ዝርዝር | መለኪያ | ከመቶ የሚይዘው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | በአለፉት ሶስት ዓመታት ምርት ልከው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ያስገኙ በዚህም መሠረት በየምርት ዓይነቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ረገድ ከ1-10ኛ ደረጃ ያላቸው፤ | ሚሊየን ዶላር | 20 |
| 2 | ከሌሎች ተፎካካሪ ላኪዎች በተሻለ ዋጋ ምርት የሸጠ ቢያንስ በአንድ መዳረሻ ገበያ በተመሳሳይ ምርት ዓይነትና ጥራት ደረጃ ከተመዘገበው አማካይ በዓለም ገበያ ዋጋ 15-20 እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ፣ | አሜሪካን ዶላር በቶን | 15 |
| 3 | ከአለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ አዳዲስ ምርት በማስተዋወቅ ኤክስፖርት እያደረገ ያለ (ቢያንስ ከአንድና ከዚያ በላይ ምርት ዓይነትና ከ10 ኮንቴነር በላይ የላከ) | ቶን/ ኮንቴነር | 10 |
| 4 | በነባር ገበያ መዳረሻ የገበያ ድርሻን እያሳደገ የመጣ ላኪ (በየዓመቱ ቢያንስ ከ5 በመቶ በላይ ያሳደገ) | ቶን አሜሪካን ዶላር | 10 |
| 5 | ወደ አዳዲስ ገበያዎች ለመግባት የገበያ ማስፋፊያ ሥራ በመስራት ምርት የሸጠ /ምርት ገገር ያፈራ (ከአንድና ከዚያ በላይ ሀገር ያስገባ) | ሀገር ቁጥር | 8 |
| 6 | በየዓመቱ ምርት አዳዲስ ገገር ደንኞችን የሳበና የሸጠ ( ቢያንስ ከአንድ በላይ አዲስ ምርት ገገር ደንበኛ የሳበና ከ10 ኮንቴነር በላይ ምርት የሸጠ) | የደንበኛ ቁጥር | 7 |
| 7 | የምርት ማዘጋጃና ማከማቻ፣ የምርት ጥራት ፍተሻ ማሽን፣ ብትን ምርትን በኮንቴነር ማሸጊያ ብሎወር ማሽን ያለው ወይም ይህንን አገልግሎት ለሌሎች በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚሰጥ ወይም የመስጠት አቅም ያለው፣ | የተለያየ መለኪያ | 5 |
| 8 | በሕገወጥ ተግባር ያልተሠማራ (ያለምክንያት ዴፎልት ያደረገ፣ የምርት ጥራትን የሚያበላሽ፣ ከዋጋ በታች የሸጠ፣ ያለአግባብ ኤክስፖርት ምርት ያከማቸ መሆን የለበትም) | ሰነድ | 5 |

| ተቁ | የመስፈርቱ ዝርዝር | መለኪያ | ከመቶ የሚይዘው ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 9 | የአጭርና የረጅም ጊዜ የቢዝነስ ዕቅድ/ ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቶ የሚንቀሳቀስ፣ | ሰነድ | 5 |
| 10 | የውስጥ አሰራርና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ የምርት ብክነትን፣ በወቅቱ አዘጋጅቶ መላክን፣ በደንበኞች ፍላጎት ላይ ተመሠረተ ጥራት፣ አስተማማኝ አቅርቦት እንዲኖር ተግቶ የሚሠራ | ልዩ ልዩ | 5 |
| 11 | የተደራጀ ቢሮና በአውቶሜሽን ስርዓት በታገዘ የመረጃ ስርዓት የሚጠቀም፣ | ልዩ ልዩ | 5 |
| 12 | ለሰራተኞቹ ፍትሃዊ የሆነ የእድገት፣ ዝውውርና የኢንሴንቲቭ አሰራርን በመዘርጋትና በመተግባር የድርጅቱን ምርታማነት እያሳደገ ያለ ላኪ መሆን አለበት፡፡ | ሰነድ | 5 |

ማጠቃለያ፡-

በዚህ ዘርፍ የተሰማራ ድርጅት በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት 12 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

## ለ. በግብርና ልማት ላይ ለተሰማሩ አምራቾች

### 1. በመሬት (እርሻ) ልማት የተሠማሩ

ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑ በግብርና ልማት የተሠማሩ ባለሀብቶች የሚመረጡበት ሥርዓት ግልጽና ለአፈጻጸም ቀላል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ የመምረጫ መስፈርቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ግብአቶችን በተሟላ መልኩ ያካተተና አሻሚ እንዳይሆን ከባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ቆይታ ጋር በተያያዘ ከገባው ውል እና ከቀረበው ቢዝነስ ፕላን አንጻር መመዘን አስፈላጊ ነው፡፡በዚሁ መሰረት የማሽነሪ አቅርቦት፣አከባቢ ጥበቃ፣የለማ መሬት፣ምርታማነት፣የካምፕ አደረጃጀት እና የሰራተኛ አያያዝን እንደ መመዘኛ መስፈርት በመያዝ መስፈርቶቹ ለኢንቨስትመንቱ ባላቸው ወሳኝ ሚና አንፃር 8 የመመዘኛ መስፈርቶች ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ሀ. የማሽነሪ አቅርቦት (10 ነጥብ)**

የአርሻዎቹ የማሽነሪ አቅርቦት የሚገመገመው አንድ ትራክተር ከተጨማሪ ወሳኝ ከሆኑ የእርሻ መሳሪያዎች (ማረሻና ዘር መዝሪያ) ጋር አንድ ትራክተር ለቡና 100 ሄክታር ለሌሎች ሰብሎች 500ሄ/ር ሁለት ትራክተር ታሳቢ በማድረግ በዚሁ አንጻር በየ 100ሄ/ርና 500ሄ/ር እጨመረ የሚሄድ ይሆናል፡፡

**ለ. የአከባቢ ጥበቃ (10 ነጥብ)**

በዚህ መመዘኛ ስር ሁለት ዋና ዋና የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ስራዎች የተካተቱ ሲሆን ነጥብ አሰጣጡ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሐ. የደን እንክብካቤ (5 ነጥብ)**

በዚህ ንኡስ መመዘኛ ስር የሚካተቱት ተግባራት፡-

- በመሬት ዝግጅት ወቅት የቀሩትን ሀገር በቀል ዛፎችን መንከባከብ፣
- አዲስ መሬት በማዘጋጀት ላይ ያሉ ደግሞ የስራ እንቅስቃሴን በማይጎዳ መልኩ ሀገር በቀል ዛፍን በማስቀረት መንከባከብ፣
- በተለያየ ምክንያት በማሳ ዝግጅት ወቅት በማሳው ላይ ምንም ዛፍ የሌለው ደግሞ ችግኝ በማዘጋጀት የመሬቱን ለምነት የመጠበቅ ስራ ሲሆን፡-
  - ✓ ይህን ስራ በአግባቡ የሰሩ 5
  - ✓ ስራው ስርተው ያላጠናቀቁ ግን ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ያሉ 2.5
  - ✓ ምንም ተግባራዊ ስራ ያላከናወኑ 0 ነጥብ ይሰጣቸዋል፡፡

**መ. የአፈር መከላትን መንከባከብ (5 ነጥብ)**

በዚህ ንኡስ መመዘኛ ስር የሚካተቱት ተግባራት፡-

- በመሬቱ ላይ ለአፈር መሸርሸር ተጋላጭ የሆኑትን የመሬት አካል በመለየት የመከላከያ ስነ ህይወታዊና ፊዚካል መከላከያዎችን መስራት፤
- ለመሬቱ ተስማሚ የአስተራረስ
- የእርከን ስራዎችን መስራት፤
- በጣም የተጎዱ አካባቢዎችን በመከለል ቦታው እንዲለማ ማድረግ

የአፈር መከላትን ከመከላከል አንጻር ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በአግባቡ ያከናወነ 5 ነጥብ፣ ስራውን ሰርተው ያላጠናቀቁ ግን ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ያሉ 2.5፣ ምንም ተግባራዊ ስራ ያላከናወኑ 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ሠ. የለማ መሬት መጠን (30 ነጥብ)

አንድ ኩባንያ በውሉ መሰረት ማልማት ከሚጠበቅበት የመሬት መጠን ውስጥ ያለማውን መሬት መቶኛ በመውሰድ ለዚህ መገምገሚያ መስፈርት ከተሰጠው ነጥብ ውስጥ ተሰልቶ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡

ረ. የምርታማነት አፈጻጸም (15 ነጥብ)

የእርሻው ምርታማነት የሚገመገመው በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተቀመጠው ምርታማነት አንፃር ሲሆን እርሻው ከአንድ ሰብል በላይ የሚያመርት ከሆነ የእያንዳንዱ ሰብል ምርታማነት ተገምግሞ አማካዩ ነጥብ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተመዘገበው ምርታማነት ከብሔራዊ ምርታማነት በላይ ከሆነ 15 ነጥብ፤
- የተመዘገበው ምርታማነት ከብሔራዊ ምርታማነት ተመጣጣኝ ከሆነ 7 ነጥብ፣
- የተመዘገበው ምርታማነት ከብሔራዊ ምርታማነት በታች ከሆነ 0 ነጥብ ይህም ማለት በተፈጥሮ አደጋ የሚከሰተውን አያካትትም

ሸ. የካምፕ አደረጃጀት (20)

ቀ. ለሰራተኛ ምቹ ሁኔታ መፈጠር (12 ነጥብ)

በዚህ መስፈርት እርሻው የሚገመገመው ለሰራተኛው በሚያቀርበው አገልግሎት ማለትም የመኖሪያ ቤት፣ የመጠጥ ውሃ፣ የህክምና አገልግሎት፤ የሽንት ቤትና ሻውር ቤት፤የመዝናኛ እና መመገቢያ አዳራሽ፣ የማብሰያ ቦታ፤ የሰራተኛ ክፍያ፤የሰራተኛ የፈጆታ እቃ አቅርቦት ሲሆኑ እንደአፈጻጸሙ ነጥብ የሚቀመጥላቸው ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት አቅርቦቱ ፡-

- የተሟላ ከሆነ - 2 ነጥብ ለእያንዳንዱ ከላይ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች የሚሰጥ ሆኖ 12 ነጥብ ያገኛል፤
- በከፊል ከሆነ - 1 ነጥብ ለእያንዳንዱ ከላይ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች የሚሰጥ ሆኖ 6 ነጥብ ያገኛል፤
- የሌለ ከሆነ - 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

በ. ለስራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር (8 ነጥብ)

በዚህ መስፈርት ወስጥ ኩባንያው በአግባቡ ኢንቨስትመንቱን እንዲመራና የገባውን ውል ለመፈጸም እንዲችል ማሟላት የሚገባውን ምቹ የስራ ሁኔታ የሚገልጹ ናቸው፡፡ እነዚህም የማዳበሪያ መጋዘን፣ የኬሚካል መጋዘን፤ የምርት መጋዘን፣ የእርሻ መሳሪያዎች መጠለያና ጋራዥ ግንባታ ሲሆኑ በዚሁ መሰረት ግንባታው፡-

- የተሟላ ከሆነ 2 ነጥብ፤ 2 ነጥብ ለእያንዳንዱ ከላይ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች የሚሰጥ ሆኖ 10 ነጥብ ያገኛል፣
- በከፊል ከሆነ 1 ነጥብ፤ 2 ነጥብ ለእያንዳንዱ ከላይ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች የሚሰጥ ሆኖ 5 ነጥብ ያገኛል
- የሌለ 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ተ. የባለሙያ አጠቃቀም (5 ነጥብ)

ይህ መመዘኛ ኩባንያው ስራውን በሙያ ረገድ አግባብነት ባላቸው ስራተኞች እየመራ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን በዚህ ረገድ አንድ እርሻ ቢያንስ አንድ ስራ አስኪያጅ፣ እንደየእርሻው ስፋት አንድ የግብርና እና አንድ የሰብል ጥበቃ ባለሙያ በመጀመሪያ ዲግሪ ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 5 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 3 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ማጠቃለያ፡- አንድ ኩባንያ በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ከገባው ውል አንጻር ያለውን የመሬት አጠቃቀም ደረጃ ለመፈረጅ ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት 6 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

2. በሆልቲካልቸር ላይ ለተሰማሩ

| ተ/ቁ | የመመዘኛው ዓይነት | መለኪያ | የተሰጠው ድርሻ ከመቶ |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| 1 | በልማት የተሸፈነ ማሳና ምርት<br>➢ በሰብል የተሸፈነ መሬት መጠን<br>➢ የሰብሉ ዓይነትና ስብጥር<br>➢ ለኤክስፖርቱ የሚቀርበው የምርት መጠን | ➢ በሰብል የተሸፈነ ማሳ ድርሻ (%)<br>➢ የድጌሬዳና የቢጋ አበባ ስብጥርና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች<br>➢ ኤክስፖርት በመቶኛ | 30 |
| 2 | የውጭ ምንዛሪ ግኝትና የሥራ ዕድል<br>➢ የውጭ ምንዛሪ መጠን<br>➢ የሥራ ዕድል | ➢ የውጭ ምንዛሪ ገቢ በሄክታር<br>➢ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኛ በሄክታር | 30 |
| 3 | መልካም የእርሻ አመራረት ዘዴ<br>➢ የተቀናጀ የመከላከያ ዘዴ አጠቃቀም<br>➢ ሠርተፍኬት | ➢ በተቀናጀ መከላከያ የተሸፈነ ሄክታር<br>➢ ለአበባ ነሐስና ሰርተፍኬት ከዚያ በላይ<br>➢ ለአትክልትና ፍራፍሬ የተቀባይ ኩባንያዎች መመዘኛዎች፣ | 15 |
| 4 | የተጨማሪ ማስፋፋትና አዳዲስ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም | ➢ የተስፋፋ መሬት በሄክታር<br>➢ ሥራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎች ብዛት | 10 |
| 5 | የመንግስት ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን የመቀበል ቁርጠኝነት | ➢ በኩልቹይን የተቀመጠውን ማዕቀፍ ማሟላት<br>➢ የአካባቢ ጥበቃና የሠራተኛ ደህንነት መሰረታዊ ፋሲሊቲ ማሟላት፣<br>➢ የውጭ ምንዛሪ ሪፖትሪየሽን ግዴታዎችን ማሟላት፣<br>➢ ለልማትና ለማህበራዊ አገልግሎት ላይ መሳተፍ | 15 |

ማጠቃለያ፡- በዚህ ዘርፍ የተሰማራ ድርጅት በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት 5 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 75 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

## 3. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት

በእንስሳት ሀብት ልማት ላይ የተሰማሩ አምራች ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚመረጡበት ሥርዓት ግልጽና አፈጻጸም ቀላል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣የመምረጫ መስፈርቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ግብአቶችን በተሟላ መልኩ ያካተተና አሻሚ እንዳይሆን ከባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ቆይታ ጋር በተያያዘ ከገባው ውል እና ካቀረበው ቢዝነስ ፕላን አንጻር የሚመዘን ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት የማሽነሪ አቅርቦት፣የማምረት አቅም፣ ለአገራችን ያስገኘው የውጪ ምንዛሪ ፣ምርታማነት፣የድርጅቱ የአስተዳደር ሁኔታ ፣የቢሮ አደረጃጀት እና የሰራተኛ አያያዝ ለኢንቨስትመንቱ ከሚኖራቸው ወሳኝ ሚና አንፃር እንደ መመዘኛ መስፈርት በመውሰድ ለየሥራ ዘርፉ እንደሚከተለው የመምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቷል፡፡

### ሀ. የሥጋ ኤክስፖርት ኢንቨስትመንት

በአሁኑ ጊዜ እያደገ ያለውን የሥጋ ኢንዱስትሪ ከፍ ለማድረግና ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ በሀገሪቱ የሚገኙ ቄራዎችን መደገፍና አዳዲስ ኢንቨስተትመንቶችን መሳብ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በኤክስፖርት ሥራ ላይ ያሉትን ቄራዎች በመለየትና ክትትል በማድረግ የምርት መጠናቸውን እንዲጨምሩ የተጠናከረ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ሲደረግ ከሚገቡ ድጋፎች መካካል አንዱ በዘርፉ ለተሰማሩ ልማታዊ ባለሀብቶች ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ይሆናል፡፡ ይህንኑ ለማስፈጸም ይረዳ ዘንድ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ሊያገኙ የሚገቡ ልማታዊ ባለሀብቶችን ለመለየት የሚያስችል ዝርዝር መስፈርት እንደሚከተው ተዘጋጅቷል፡፡

1. የማሽነሪ አቅርቦት (15 ነጥብ)

የማሽነሪ አቅርቦት የሚገመገመው ወሳኝ ከሆኑ መሳሪያዎች ለሥጋ ማምረት የሚውሉ ታሳቢ በማድረግ በዚሁ መሰረት ከሚያመርተው ምርት አንጻር እጨመረ የሚሄድ ሆኖ ከተያዘው የልማት እቅድ አንጻር አቅርቦቱ ታይቶ ነጥቡ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

2. የማምረት ዓቅም (10 ነጥብ)

አንድ ኤክስፖርት ቄራ በውሉና በዕቅዱ መሰረት ሥጋና የሥጋ ውጤቶችን በማቀነባበር የማምረት ዓቅም መሰረት ተደርጎ በአማካይ የወር ምርት ማምረት ከሚጠበቅበት መጠን ውስጥ

ያመረተውን ምርት መቶኛ በመውሰድ ለዚህ መገምገሚያ መስፈርት ከተሰጠው ነጥብ ውስጥ ተሰልቶ የሚቀመጥለት ይሆናል።

3. የኤክስፖርት መጠንና ለአገር የሚያስገባው የውጪ ምንዛሬ (20 ነጥብ)

የቁራው ምርታማነት የሚገመገመው በዕቅድ ላይ ከተቀመጠው ምርታማነት አንፃር ሲሆን የኤክስፖርት መጠንና ለአገር የሚያስገባው የውጪ ምንዛሬ ተገምግሞ አማካዩ ነጥብ የሚቀመጥለት ይሆናል። በዚሁ መሰረት፡-

- የተመዘገበው የኤክስፖርት መጠንና ለአገር የሚያስገባው የውጪ ምንዛሬ በታቀደው መሰረትና ከዚያ በላይ ከሆነ 20 ነጥብ፤
- የተመዘገበው የኤክስፖርት መጠንና ለአገር የሚያስገባው የውጪ ምንዛሬ በዕቅዱ ላይ ከተገለፀው 10% ካነሰ 15 ነጥብ፤
- የተመዘገበው የኤክስፖርት መጠንና ለአገር የሚያስገባው የውጪ ምንዛሬ በዕቅዱ ላይ ከተገለፀው ምርታማነት 20% ካነሰ 10 ነጥብ፤
- ተመዘገበው የኤክስፖርት መጠንና ለአገር የሚያስገባው የውጪ ምንዛሬ በዕቅዱ ላይ ከተገለጸው ከ20% በላይ ካነሰ 0 ነጥብ፤

4. በምግብ ደህንነት ጥራትና አመራረት ላይ ያለው አለም አቀፍ ስታንዳርድ (ISO Certeficate) በገዢ አገሮች ያለው ተቀባይነት (15)

5. በመንግስት በኩል ለሚቀርብ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ (5 ነጥብ)

6. አርብቶ አደር ተጠቃሚ ያደረገ የእንስሳት ግዢ ስርዓት ያለው (5 ነጥብ)
7. ድርጅቱ የፈጠረው የሥራ ዕድል (10 ነጥብ)

8. የቁራው አስተዳደር፣ የቢሮ አደረጃጀትና ለሰራተኛ ምቹ ሁኔታ መፍጠር (15 ነጥብ)

በዚህ መስፈርት ድርጅቱ የሚገመገመው ለሰራተኛው በሚያቀርበው አገልግሎት ሲሆን እነዚህም የመኖሪያ ቤት፣ የመጠጥ ውሃ፣ ህክምና አገልግሎት፤ የሽንት ቤትና ሻውር ቤት፤የመዝናኛ እና መመገቢያ አዳራሽ፣ ማብሰያ ቦታ፤ የሰራተኛ ክፍያ፤የሰራተኛ የፍጆታ እቃ አቅርቦት ሲሆኑ እንደአፈጻጸሙ ነጥብ የሚቀመጥላቸው ይሆናል። በዚሁ መሰረት አቅርቦቱ ፡-

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 3 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 2 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡

9. የባለሙያ አጠቃቀም (5 ነጥብ)

ይህ መመዘኛ ድርጅቱ ስራውን በሙያ ረገድ አግባብነት ባላቸው ሰራተኞች እየመራ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻልበት ሲሆን በዚህ ረገድ አንድ ድርጅት ቢያንስ አንድ ስራ አስኪያጅ፣ እንደ የድርጅቱ ስፋት ባለሙያዎች ሊኖረው ይገባል።በዚሁ መሰረት፡-

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 5 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 3 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ማጠቃለያ፡- በዚህ ዘርፍ የተሰማራ ድርጅት በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት 9 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

## ለ. የቁም እንስሳት ማድለብና ኤክስፖርት ማድረግ ኢንቨስትመንት

የቁም እንስሳት አድላቢዎችና ኤክስፖርተሮች በእንስሳት ሀብት የሥራ ዘርፍ የተሠማሩ የግል ድርጅቶችን የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሆነው እንዲሰየሙ ለመምረጥ የሚያስችሉ መስፈርቶች (32 ነጥብ)

1. የወጪ ንግዱ የአሰራር ሂደት (65 ነጥብ)
   - ድርጅቱ ያስገባው የውጪ ምንዛሪ መጠን (30 ነጥብ)
   - የሀብት አመራር ስርዓት እና ያላቸው ደረጃውን የጠበቀ የማቆያ ቦታ (10 ነጥብ)
   - ከተቀባይ ሀገራት ገዢዎች ጋር ያለው መልካም ግንኙነትና ኮንትራቶችን የመፈፀም ብቃት (10 ነጥብ)
   - በህገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግድ ተሳታፊ ያለመሆንና ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር ያሳዩት የተግባር እንቅስቃሴ (5 ነጥብ)
   - ድርጅቱ ያለው የፋይናንስ አቅም (5 ነጥብ)
   - የሚጠበቅባቸውን የመንግስት ግብርና ቀረጥ በወቅቱ በመክፈላቸው (5 ነጥብ)

2. የማድለብ ዓቅም (10 ነጥብ)

አንድ አድላቢ በዕቅዱ መሰረት ማድለብ ከሚጠበቅበት የእንስሳት መጠን ውስጥ ያደለባቸውን መቶኛ በመውሰድ ለዚህ መገምገሚያ መስፈርት ከተሰጠው ነጥብ ውስጥ ተስልቶ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡ አድላቢው የሚገመገመው በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተቀመጠው ዕቅድ አንፃር ሲሆን ምርታማነቱ ተገምግሞ አማካዩ ነጥብ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ መሰረትና ከዚያ በላይ ከሆነ 10 ነጥብ፤
- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለፀው 10% ካነሰ 10 ነጥብ፤

- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለፀው ምርታማነት 20% ካነሰ 5 ነጥብ፤
- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለጸው ከ20% በላይ ካነሰ 0 ነጥብ፤

3. በመንግስት በኩል ለሚቀርብ ጥያቄ ፈጣን መምላሽ የሚሰጥ (5 ነጥብ)
4. አርብቶ አደር ተጠቃሚ ያደረገ የእንስሳት ግዢ ስርዓት ያለው (5 ነጥብ)
5. ድርጅቱ የፈጠረው የሥራ ዕድል (10 ነጥብ)
6. የቢሮ አደረጃጀትና ለሰራተኛ ምቹ ሁኔታ መፍጠር (5 ነጥብ)

በዚህ መስፈርት ድርጅቱ የሚገመገመው ለሰራተኛው በሚያቀርበው አገልግሎት ሲሆን እነዚህም የመኖሪያ ቤት፣ የመጠጥ ውሃ፣ ህክምና አገልግሎት፤ የሽንት ቤትና ሻውር ቤት፤የመዝናኛ እና መመገቢያ አዳራሽ፣ ማብሰያ ቦታ፤ የሰራተኛ ክፍያ፤የሰራተኛ የፍጆታ እቃ አቅርቦት ሲሆኑ እንደአፈጻጸሙ ነጥብ የሚቀመጥላቸው ይሆናል። በዚሁ መሰረት አቅርቦቱ ፡-

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 5 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 3 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል።

ማጠቃለያ፡- አንድ ኩባንያ በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደም ሲል ለተዘረዘሩት 6 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል።

ሐ. ወተት ማቀነባበርና የወተት ውጤቶችን ማምረት

በወተትና ወተት ተዋፅኦ ማቀነባበር ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች በአሁኑ ሰዓት ፋብሪካዎቹ ከተለያዩ አካባቢዎች ጥሬ ወተት በማሰባሰብ አቀነባብሮ ለገበያ ማቅረብ የሚችሉት የወተቱ ጥራት ተጠብቆና አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ እንዲሁም የሚመረተውን ወተት በጥራት ወደ ገበያ ማሰራጨት ሲችሉ ነው።

1. ወተት የማቀነባበር ዓቅም (25 ነጥብ)

አንድ ወተት ማቀነባበርያ ላይ የሚሰራ ካምፓኒ ማቀነባበር ከሚጠበቅበት የወተት መጠን ውስጥ ያቀነባበረውን ወተት መቶኛ በመውሰድ ለዚህ መገምገሚያ መስፈርት ከተሰጠውን ነጥብ ውስጥ ተሰልቶ የሚቀመጥለት ይሆናል። ወተት ማቀነበባበር

- ✓ 2000 ሊትር - 8000 ሊትር የማምረት አቅም ላላቸው (10 ነጥብ)
- ✓ 8001 ሊትር - 25000 ሊትር (15 ነጥብ)
- ✓ ከ25000 ሊትር በላይ (25 ነጥብ)

2. የማሽነሪ አቅርቦት (20 ነጥብ)

የማሽነሪ አቅርቦት የሚገመገመው ወሳኝ ከሆኑ መሳሪያዎች ለወተት ማቀነባበር የሚሆኑ ታሳቢ በማድረግ በዚሁ መሰረት ከሚያቀነባበሩት ወተት አንጻር እጨመረ የሚሄድ ሆኖ ከተያዘው የልማት እቅድ አንጻር አቅርቦቱ ታይቶ ነጥቡ የሚሰጥ ይሆናል።

3. ድርጅቱ የፈጠረው የሥራ ዕድል (10 ነጥብ)

4. የቢሮ አደረጃጀትና ለሰራተኛ ምቹ ሁኔታ መፍጠር (15 ነጥብ)

በዚህ መስፈርት ድርጅቱ የሚገመገመው ለሰራተኛው በሚያቀርበው አገልግሎት ሲሆን እነዚህም የመኖሪያ ቤት፣ የመጠጥ ውሃ፣ ህክምና አገልግሎት፤ የሽንት ቤትና ሻውር ቤት፤የመዝናኛ እና መመገቢያ አዳራሽ፣ ማብሰያ ቦታ፤ የሰራተኛ ክፍያ፤የሰራተኛ የፍጆታ እቃ አቅርቦት ሲሆኑ እንደአፈጻጸሙ ነጥብ የሚቀመጥላቸው ይሆናል። በዚሁ መሰረት አቅርቦቱ ፦

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 5 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 3 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል።

5. በመንግስት በኩል ለሚቀርብ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ (5 ነጥብ)

6. የድርጅቱ የአስተዳደር ሁኔታ (20 ነጥብ)

7. የባለሙያ አጠቃቀም (5 ነጥብ)

ይህ መመዘኛ ድርጅቱ ስራውን በሙያ ረገድ አግባብነት ባላቸው ሰራተኞች እየመራ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻልበት ሲሆን በዚህ ረገድ አንድ ድርጅት ቢያንስ አንድ ስራ አስኪያጅ፣ እንደ የድርጅቱ ስፋት ባለሙያዎች ሊኖረው ይገባል። በዚሁ መሰረት፦

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 5 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 3 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ማጠቃለያ፡-

አንድ ኩባንያ በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደም ሲል ለተዘረዘሩት 7 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

መ. የወተት ከብት እርባታ ኢንቨስትመንት

በአሁኑ ወቅት በአገራችን በወተት ከብት እርባታ በኢንቨስትመንት ደረጃ ያሉትን ባለሀብቶች ያላቸውን የእንስሳት ብዛት ከ100-200 እና ከ200 በላይ ያላቸው

1. ወተት የማምረት ዓቅም (30 ነጥብ)

አንድ ባለሀብት መያዝ ከሚጠበቅበት የወተት ላሞች መጠን ውስጥ ያለውን ብዛት መቶኛ በመውሰድ ለዚህ መገምገሚያ መስፈርት ከተሰጠውን ነጥብ ውስጥ ተሰልቶ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡በአሁኑ ወቅት ያለውን የወተት አቅርቦት እጥረት ለመቀነስ በሚያግዝ የወተት ከብት እርባታ ስራ የሚሰራ

- 100-200 (20. ነጥብ)
- ከ 200 በላይ (30 ነጥብ)

2. የምርታማነት አፈጻጸም (25 ነጥብ)

የድርጅቱ ምርታማነት የሚገመገመው በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተቀመጠው ምርታማነት አንፃር ሲሆን ምርታማነቱ ተገምግሞ አማካዩ ነጥብ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ መሰረትና ከዚያ በላይ ከሆነ 25 ነጥብ፤
- ተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለፀው 10% ካነሰ 15 ነጥብ፤
- ተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለፀው ምርታማነት 20% ካነሰ 10 ነጥብ፤
- ተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለጸው ከ20% በላይ ካነሰ 0 ነጥብ፤

3. ድርጅቱ የፈጠረው የሥራ ዕድል (10 ነጥብ)

4. የቢሮ አደረጃጀትና ለሰራተኛ ምቹ ሁኔታ መፍጠር (15 ነጥብ)

በዚህ መስፈርት ድርጅቱ የሚገመገመው ለሰራተኛው በሚያቀርበው አገልግሎት ሲሆን እነዚህም የመኖሪያ ቤት፣ የመጠጥ ውሃ፣ ህክምና አገልግሎት፤ የሽንት ቤትና ሻውር ቤት፤የመዝናኛ እና መመገቢያ አዳራሽ፣ ማብሰያ ቦታ፤ የሰራተኛ ክፍያ፤የሰራተኛ የፍጆታ እቃ አቅርቦት ሲሆኑ እንደአፈጻጸሙ ነጥብ የሚቀመጥላቸው ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት አቅርቦቱ ፡-

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 5 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 3 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

5. በመንግስት በኩል ለሚቀርብ ጥያቄ ፈጣን መምላሽ የሚሰጥ (5 ነጥብ)

6. የድርጅቱ የአስተዳደር ሁኔታ (10 ነጥብ)

7. የባለሙያ አጠቃቀም (5 ነጥብ)

ይህ መመዘኛ ድርጅቱ ስራውን በሙያ ረገድ አግባብነት ባላቸው ሰራተኞች እየመራ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻልበት ሲሆን በዚህ ረገድ አንድ ድርጅት ቢያንስ አንድ ስራ አስኪያጅ፣ እንደ የድርጅቱ ስፋት ባለሙያዎች ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 5 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 3 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ማጠቃለያ፡-

አንድ ኩባንያ በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት 7 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

ሠ. የእንስሳት መኖ ማምረት እርሻ ልማት ኢንቨስትመንቶች

የእንስሳት መኖ ለእንስሳት እርባታ፣ ለወተት ልማት፣ ለእንስሳት ማድለብ እንዲሁም ጥራት ያለው ሥጋ ለኤክስፖርት ለማቅረብ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው:: :: ከዚህ ጋር ተያይዞ በአሁኑ ወቅት ያለው የመኖ ምርት ፍላጎትና አቅርቦት እንዲሁም ዋጋው የተመጣጠነ እንዲሆን በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መስፈርቱ ተግባራዊ ማድረጉ ወሳኝ ነው::

1. የፕሮጀክት የማምረት ዓቅም (25 ነጥብ)
2. መኖ ለማምረት የሚለማው መሬት ስፋት በሄክታር (25 ነጥብ)
    - 200-300 ሄ/ር (5 ነጥብ)
    - 301-1000 ሄ/ር (7 ነጥብ)
    - 1001-2000ሄ/ር (10 ነጥብ)
    - 2001 -3000ሄ/ር (15 ነጥብ)
    - 3001-4000 ሄ/ር (20 ነጥብ)
    - ከ4000 ሄ/ር በላይ (25 ነጥብ)
3. በመንግስት በኩል ለሚቀርብ ጥያቄ ፈጣን መምላሽ የሚሰጥ (5 ነጥብ)
4. የድርጅቱ የአስተዳደር ሁኔታ (20 ነጥብ)
5. የባለሙያ አጠቃቀም (5 ነጥብ)
6. የፈጠረው የስራ ዕድል ብዛት (20 ነጥብ)

ማጠቃለያ፡-

አንድ ኩባንያ በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት 6 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል::

ረ. የእንስሳት መኖ ማቀነባበር

ከእንስሳት መኖ ልማት ጋር ተያይዞ የእንስሳት መኖ የማቀነባበር ሥራ የሚሰሩ ባለሀብቶች

1. የማቀነባበር ዓቅም (25 ነጥብ)

አንድ መኖ ማቀነባበርያ ፋብሪካ በዕቅዱ መሰረት ማቀነባበር ከሚጠበቅበት የመኖ መጠን ውስጥ ያቀነባበረውን መኖ መቶኛ በመውሰድ ለዚህ መገምገሚያ መስፈርት ከተሰጠውን ነጥብ ውስጥ ተሰልቶ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡

2. የምርታማነት አፈጻጸም (25 ነጥብ)

የድርጅቱ ምርታማነት የሚገመገመው በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተቀመጠው ምርታማነት አንፃር ሲሆን ምርታማነቱ ተገምግሞ አማካዩ ነጥብ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ መሰረትና ከዚያ በላይ ከሆነ 25 ነጥብ፤
- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለፀው 10% ካነሰ 15 ነጥብ፤
- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለፀው ምርታማነት 20% ካነሰ 5 ነጥብ፤
- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለጸው ከ20% በላይ ካነሰ 0 ነጥብ፤

3. የማሽነሪ አቅርቦት (15 ነጥብ)

የማሽነሪ አቅርቦት የሚገመገመው ወሳኝ ከሆኑ መሳሪያዎች ታሳቢ በማድረግ በዚሁ መሰረት ከሚያቀነባብረው አንጻር እጨመረ የሚሄድ ሆኖ ከተያዘው የልማት እቅድ አንጻር አቅርቦቱ ታይቶ ነጥቡ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

4. ድርጅቱ የፈጠረው የሥራ ዕድል (10 ነጥብ)

5. የቢሮ አደረጃጀትና ለሰራተኛ ምቹ ሁኔታ መፍጠር (15 ነጥብ)

በዚህ መስፈርት ድርጅቱ የሚገመገመው ለሰራተኛው በሚያቀርበው አገልግሎት ሲሆን እነዚህም የመኖሪያ ቤት፣ የመጠጥ ውሃ፣ ህክምና አገልግሎት፤ የሽንት ቤትና ሻውር ቤት፤የመዝናኛ እና መመገቢያ አዳራሽ፣ ማብሰያ ቦታ፤ የሰራተኛ ክፍያ፤የሰራተኛ የፍጆታ እቃ አቅርቦት ሲሆኑ እንደአፈጻጸሙ ነጥብ የሚቀመጥላቸው ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት አቅርቦቱ ፡-

- የተሟላ እና ለባለሙያ ምቹ ሁኔታና የቢሮ አደረጃጀት ያለው15 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 10 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

6. የባለሙያ አጠቃቀም (10 ነጥብ)
ይህ መመዘኛ ድርጅቱ ስራውን በሙያ ረገድ አግባብነት ባላቸው ሰራተኞች እየመራ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻልበት ሲሆን በዚህ ረገድ አንድ ድርጅት ቢያንስ አንድ ስራ አስኪያጅ፣ እንደ የድርጅቱ ስፋት ባለሙያዎች ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 10 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 5 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ማጠቃለያ፡-

አንድ ኩባንያ በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት 6 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

## ሸ. የዶሮ እርባታ ኢንቨስትመንት

በዶሮ እርባታና ማቀነባበር ኢንቨስትመንት ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የተቀመጠውን መስፈርት

1. የማምረት ዓቅም (15 ነጥብ)

አንድ ኩባንያ በዕቅዱ መሰረት ማርባት ከሚጠበቅበት የዶሮ ብዛት መጠን ውስጥ ያረባውን ደሮ መቶኛ በመውሰድ ለዚህ መገምገሚያ መስፈርት ከተሰጠውን ነጥብ ውስጥ ተሰልቶ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡

2. የፕሮጀክት ዓቅም(15 ነጥብ) በእንስሳት ብዛት ሲሆን የዶሮ እርባታና ተዋፅኦ ልማት
   - 2000-10000 (5 ነጥብ)
   - 10001-50000 (10 ነጥብ)
   - ከ 50000 በላይ (15 ነጠብ)
3. የምርታማነት አፈጻጸም (20 ነጥብ)

የድርጅቱ ምርታማነት የሚገመገመው በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተቀመጠው ምርታማነት አንፃር ሲሆን ምርታማነቱ ተገምግሞ አማካዩ ነጥብ የሚቀመጥለት ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ መሰረትና ከዚያ በላይ ከሆነ 20 ነጥብ፤
- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለፀው 10% ካነሰ 15 ነጥብ፤
- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለፀው ምርታማነት 20% ካነሰ 10 ነጥብ፤

- የተመዘገበው ምርታማነት በቢዝነስ ፕላኑ ላይ ከተገለጸው ከ20% በላይ ካነሰ 0 ነጥብ፤

4. የማሽነሪ አቅርቦት (15 ነጥብ)

የማሽነሪ አቅርቦት የሚገመገመው ወሳኝ ከሆኑ መሳሪያዎች ለዶሮ እርባታ የሚሆኑ ታሳቢ በማድረግ በዚሁ መሰረት ከሚረባው አንጻር እጨመረ የሚሄድ ሆኖ ከተያዘው የልማት እቅድ አንጻር አቅርቦቱ ታይቶ ነጥቡ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

5. ድርጅቱ የፈጠረው የሥራ ዕድል (10 ነጥብ)

6. የቢሮ አደረጃጀትና ለሰራተኛ ምቹ ሁኔታ መፍጠር (15 ነጥብ)

በዚህ መስፈርት ድርጅቱ የሚገመገመው ለሰራተኛው በሚያቀርበው አገልግሎት ሲሆን እነዚህም የመኖሪያ ቤት፣ የመጠጥ ውሃ፣ ህክምና አገልግሎት፤ የሽንት ቤትና ሻውር ቤት፤የመዝናኛ እና መመገቢያ አዳራሽ፣ ማብሰያ ቦታ፤ የሰራተኛ ክፍያ፤የሰራተኛ የፍጆታ እቃ አቅርቦት ሲሆኑ እንደአፈጻጸሙ ነጥብ የሚቀመጥላቸው ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት አቅርቦቱ ፡-

- የተሟላ እና ለባለሙያ ምቹ ሁኔታና የቢሮ አደረጃጀት ያለው15 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 10 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

7. የባለሙያ አጠቃቀም (10 ነጥብ)

ይህ መመዘኛ ድርጅቱ ስራውን በሙያ ረገድ አግባብነት ባላቸው ሰራተኞች እየመራ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻልበት ሲሆን በዚህ ረገድ አንድ ድርጅት ቢያንስ አንድ ስራ አስኪያጅ፣ እንደ የድርጅቱ ስፋት ባለሙያዎች ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

- የተሟላ ባለሙያ ያለው 15 ነጥብ፤
- በከፊል ያለው 10 ነጥብ፤
- ምንም የሌለው 0 ነጥብ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ማጠቃለያ፡-

አንድ ኩባንያ በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት 7 የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

### 3.1.5 በማዕድን ማምረት እና ወደ ውጪ መላክ ለተሰማሩ

በማዕድን ማምረት እና ወደ ውጪ መላክ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት በመመዘን መስፈርቱን የሚያሟሉትን የመለየት እና ለባለሥልጣኑ የማሳወቅ ሥራ የሚያከናውነው በማዕድን ሚኒስቴር ይሆናል። ለዚሁ ይረዳ ዘንድ ለአርፉ የሚከተለው ዝርዝር የመምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቷል።

1. ለሁሉም ዓይነት ፈቃዶች የሚያገለግሉ መሥፈርቶች

   ሀ. በፔትሮሊየም ሕግ መሠረት ግዴታውን በአግባቡ በመወጣት ላይ የሚገኝ

   - ሥራውን በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት የሚያከናውን፣
   - የሚፈለግበትን ሪፖርት እና የሥራ ፕሮግራም በወቅቱ የሚያቀርበ፣
   - የሚፈለግበትን የክፍያ ግዴታዎች በወቅቱ የሚወጣ፣

   ለ. ለሥራው ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ካፒታል የመደበ

   ሐ. በተሠማራበት የፔትሮሊየም ፍለጋ ሥራ የፈጠረው የሥራ ዕድል

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት መሥፈርቶች በተጨማሪ እንደ ሥራው ዓይነት የሚከተሉት መሥፈርቶች በመመዘኛነት ጥቅም ላይ ውለዋል፤

2. ለፔትሮሊየም ፍለጋና ጥናት ሥራ ብቻ የሚያገለግሉ መሥፈርቶች

   ሀ. በላቀ የፍለጋ ሥራ ላይ የሚገኝ

   - ለሳይስሚክ ሥራ ዝግጅት ያደረገ፣
   - በፈቃድ ዓመቱ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ (ድሪሊንግ) ሥራ ለመሥራት ዝግጅት ያደረገ እና
   - የአዋጭነት (fesibility) ጥናት በመሥራት ላይ የሚገኝ ወይም ያፀደቀ

   ለ. በፈቃድ ዓመቱ የመሬት (Ground) የአየር (Airborn) ጂኦፊዚክስና ጂኦሎጂ ሥራ በመሥራት ላይ የሚገኝ ወይም ያቀደ፣

3. ለፔትሮሊየም ፍለጋና ልማት ሥራ ብቻ የሚያገለግሉ መሥፈርቶች

   ሀ. ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለአገሪቱ የሚያስገኙ የፔትሮሊየም ፍለጋና ልማት ሥራ ላይ የተሠማራ፣

   ለ. በከፍተኛ ወጪ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት የሚያስችል ለተለያዩ ዘርፎች በግብአትነት የሚያገለግሉ ምርት ሥራ ላይ የተሠማራ


ማጠቃለያ፡-

አንድ ኩባንያ በልማታዊ ባለሀብትነት ተመርጦ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ጥቅም የሚያስገኝ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ቀደሚ ሲል ለተዘረዘሩት

የመምረጫ መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሰጠው 100 ነጥብ ውስጥ ከእያንዳንዱ መመዘኛ አንጻር ያገኛቸው ነጥብ ተደምሮ 60 እና ከዚያ በላይ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

## 3.2. ቀላል የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ተጠቃሚነት ሰርተፍኬት የሚሰጥበት የሥራ ሂደት

### 3.2.1.ቀላል የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ተጠቃሚነት ሰርተፍኬት የሚሰጥበት ስርዓት ስዕላዊ መግለጫ፣



3.2.2.ቀላል የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ተጠቃሚነት ሰርተፍኬት የሚሰጥበት ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | ፈፃሚ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | **ማመልከቻ ማቅረብ፡-**<br>ማንኛውም በምርት ተግባር የተሰማራ አምራች ይህንን ስርዓት ለመጠቀም ሲፈልግ ያለምንም ገደብ ማመልከቻውን በፅሁፍ ለሚመለከተው አስፈጻሚ መ/ቤት ማቅረብ፣ | አምራች | - |
| 2 | **የመመዘኛ መስፈርት ቼክሊስት መስጠት፡-**<br>የአምራች ማመልከቻ እንዲቀርብ ለዚሁ አገልግሎት ለማግኘት ቅድሚያ ሊሟሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች ዝርዝር የያዘ "Self-evaluation form" በመስጠት ማመልከቻውን መዝግቦ መያዝ፣ | አስፈጻሚ መ/ቤት | - |
| 3 | **"Self-evaluation form" በአግባቡ መሞላቱን እና አባሪ ሰነዶችን ማረጋገጥ፡-**<br>• አመልካቹ በተሰጠው "Self-evaluation form" መሠረት መረጃዎቹን ሞልቶና አባሪ ሠነዶችን አያይዞ ካቀረበ የተሞሉት መረጃዎችን ከአባሪ ሠነዶችና በአካላዊ ጉብኝት በመገምገም ትክክለኛነታቸውና አግባብነታቸውን ማረጋገጥ፣<br>• መስፈርቶችን ያላሟሉ ከሆነ ምክንያቱን በፅሁፍ ማሳወቅ፣<br>• መስፈርቶችን ካሟላ ቀጣይ ሂደት ማከናወን፣ | አስፈጻሚ መ/ቤት | 5 የስራ ቀናት ውስጥ |
| 4 | **በአመልካቹ ስም የተደራጀ ፋይል ማደራጀት፡-**<br>የቀረበው የመገምገሚያ መስፈርት በሚፈለገው መልኩ የተሟላ በመሆኑ በአምራቹ ስም ቋሚ የሆነ የመረጃ መያዣ የተደራጀ ፋይል ማዘጋጀት (ያመለከተበት ቀን፣ የተመለሰበት ቀን፣ ስለመረጃዎች ትክክለኛነት የአገልግሎቱ አይነት ወዘተ...) | አስፈጻሚ መ/ቤት | - |

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | ፈፃሚ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 5 | የውሳኔ ሃሳብ የያዘ አስተያየት ለበላይ አካል ማቅረብ፣<br>• በቀረበውና በተረጋገጠው የመገምገሚያ መስፈርት መሠረት አመልካቹ /አምራቹ ሊያገኝ የሚገባውን ቀላል የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ስርዓት በመግለፅና ተጨማሪ የባለሙያ አስተያየት በማካተት የውሳኔ ሃሳብ ለበላይ አካል ማቅረብ፡-<br>• የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ አስተያየት ተቀባይነት ካላገኘ ሊስተካከሉ የሚገቡ ጉዳዮችን ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ፣<br>• የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ አስተያየት ተቀባይነት ካገኘ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚደርገው ሠርተፍኬት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ በበላይ አመራር በሚ/ር ወይም በሚ/ር ዴኤታ በተፈረመ በደብዳቤ ማሳወቅ፣<br>• በደርጅቱ ሥም በተከፈተው ፋይል ላይ የደብዳቤውን ኮፒ ፋይል ማድረግ፣ | አስፈጻሚ መ/ቤት | አካላዊ ግምገማ በተደረገ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ |
| 6 | ሠርተፍኬት መስጠት፡-<br>• ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚነት እንዲሰጥ የተጠየቀበት ደብዳቤ ሲደርስ መዝግቦ በድርጅቱ ሥም ፋይል መክፈት፣<br>• ድርጅቱ ነባር ከሆነ የድርጅቱን የታክስና ጉምሩክ አፈጻጸም ጤናማነት በማጣራት ማረጋገጥ፣<br>• የድርጅቱን የታክስና ጉምሩክ አፈጻጸም ጤናማ ሆኖ ከተገኘ ሠርተፊኬት ማዘጋጀት፣<br>• የተዘጋጀውን ቀላል የጉምሩክ ዕቃ አወጣጥ ተጠቃሚነት ሰርተፍኬት በማስፈረም ለተጠቃሚው መስጠት፣ | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | ደብዳቤው በደረሰ በ7 የስራ ቀናት ውስጥ |

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | ፈፃሚ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 7 | **ለሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ማሳወቅ፣**<br>የተጠቃሚነቱን ሠርተፍኬት ያገኙ አምራቾች ዝርዝርና የሠርተፍኬቱን ኮፒ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እና የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ማሳወቅ፣ | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | ሠርተፊኬቱ በተፈረመ በአንድ ቀን ውስጥ |
| 8 | **ስለ አፈፃፀሙ ከባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት ግብረ መልስ መቀበልና ፕሮፋይል ማደስ፣**<br>አምራቹ በተሠጠው መብት መሠረት በአግባቡ ስለመጠቀሙ ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች ግብረ-መልስ በማሰባሰብ በተከፈተለት ፋይል ላይ መረጃውን ማስፈር፣ | አስፈጻሚ መ/ቤት | - |
| 9 | **በግብረ መልሱ መሠረት አስፈላጊውን ቁጥጥር ማድረግ፣**<br>ከባለሥልጣኑ መ/ቤት ስለ ባለመብቱ ድርጅት አፈፃፀም በተሰጠው ግብረ-መልስ መሠረት በሠርተፊኬቱ እደሳ ወቅት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣ | አስፈጻሚ መ/ቤት | - |
| 10 | ከአስፈጻሚ መ/ቤት የእደሳ ደብዳቤ ሲደርስ ባለስልጣኑ በራሱ ከያዘው መረጃ ጋር በማገናዘብ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው ሠርተፊኬቱን ያድሳል፣ | የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | - |

## 4.የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬትይዘት

የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚዘጋጅ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች የሚያካትት ይሆናል። (የምስክር ወረቀቱ ናሙና ከዚህ ጥናት ጋር ተያይዟል)።

- የተመረጠው ድርጅት ስም፤
- የታክስ መለያ ቁጥር(Tax Idntification Number)፤
- ድርጅቱ የተሰማራበት ዘርፍ(sector)፤እና
- የሰርቲፊኬት ቁጥር።

የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት የሚሰጠው በኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን፣ ባለሥልጣኑ ሠርተፊኬቱን የሚሠጠው አስፈጻሚ መ/ቤቶች በክፍል

3.2. ላይ በየዘርፉ ተለይቶ በተቀመቀጠው መምረጫ መስፈርቶች መሠረት መዝነው የመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ለሚያሳውቁት ድርጅት ይሆናል፡፡ የሚሰጠው ሠርተፊኬት ተከታታይነት ያለው ባለአራት (4) ድጂት ቁጥር እና ድርጅቱ ከተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ጋር በተያያዘ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግለት የመንግስት አስፈጻሚ መ/ቤትን የሚያመላክት 3 ፊደላት የሚኖረው ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | ሠርተፊኬቱን የሰጠው ተቋም | የሠርተፊኬት ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | MOI/0001 |
| 2 | የግብርና ሚኒስቴር | MOA/0001 |
| 3 | የንግድ ሚኒስቴር | MOT/0001 |
| 4 | የማዕድን ሚኒስቴር | MOM/0001 |

የሚሰጠው የሰርተፊኬት ቁጥር ለባለመብቱ ተገቢውን ደጋፍ፣ክትትልና ቁጥጥር ለማደረግ፣ሥርዓቱን በአውቶሜሽን ለመደገፍና መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ በመያዝ ለሪፖርት ዝግጅት እና ለቀጣይ ውሳኔዎች መጠቀም የሚያስችል የተጠቃሚው መለያ ቁጥር ስለሆነ፣ የቁጥር አሰጣጡ ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሠርተፊኬቱ ጀርባ ላይ የተጠቃሚው መብትና ግዴታዎች በዝርዝር የሚጠቀስ ይሆናል፡፡

## 5.የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚያስገኘው ጠቀሜታ እና የሚያስከትለው ግዴታ

### 5.1የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚያስገኘው ጠቀሜታ

የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ከማሳካት አንጻር ከፍተኛ ሚና ያለውን ልማታዊ ባለሀብት ቀደም ሲል በተዘረዘረው የመምረጫ መስፈርት በመለየት የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ ሠርተፊኬት የተሰጠው ልማታዊ ባለሀብት የተቋቋመበትን ዓላማ ከማስካት አንጻር ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገባው እና ከሀገር ለሚያስወጣው ዕቃ በልዩ ሁኔታ የተፋጠነ የጉምሩክ አገልግሎት የሚያገኝበት አዲስ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት ተቀርጿል፡፡ የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ለባለመብቱ በአዲሱ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓት የተካተቱትን የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች የሚያስገኝ ይሆናል፡-

- በዝቅተኛ ሥጋት ደረጃ ተመድበው ፈጣን አገልግሎት የማግኘት፤
- ከሰነድ ምርመራ እና ፍተሻ ጋር በተያያዘ እንደአስፈላጊነቱ የሚደረግ የጉምሩክ ቁጥጥር የቅድሚያ አገልግሎት የማግኘት፤
- የፍተሻ አገልግሎት በራሱ በተጠቃሚው መጋዘን የማግኘት፤
- በዝቅተኛ የቅድመ ዕቃ አወጣጥ የጉምሩክ ቁጥጥር እና ጣልቃ ገብነት የመስተናገድ፤
- ቅድመ ዕቃ አወጣጥ (Prearrival clearance) የጉምሩክ ስነስርዓት መፈፀም ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን፤
- የሚያቀርቡት አቤቱታና ቅሬታ በቅድሚያ እንዲታይ የሚደረግበት ሁኔታ የማግኘት፤እና
- ባቀረቡት ኢንቮይስ መሰረት እንዲስተናገዱ ማድረግ እና በቀጣይ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እንደ አስፈላጊነቱ የሚታይበት ሁኔታ።

ከዚህም በተጨማሪ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ለሚጠቀሙ ከመልቲ ሞዳል ኦፕሬተሩ የቅድሚያ የሎጀስቲክ አገልግሎት የማግኘት ጠቀሜታ ይኖረዋል። በዚህም የባለሃብቱ ዕቃ በወደብ ላይ የሚኖረው ቆይታ እንዲሁም ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ሲባል ዕቃው በጉምሩክ ቁጥጥር ስር የሚቆይበት ጊዜ በእጅጉ እንዲያጥር የሚያደርግ በመሆኑ የባለሀብቱን በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነቱን ያሳድጋል። ይህም ባለሀብቱ የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ከማሳካት አንጻር የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ያስችለዋል።

## 5.2.ዕውቅና ሠርተፍኬት የተሰጠው የሚኖርበት ግዴታ

የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት የተሰጠው ልማታዊ ባለሀብት ከፍ ሲል በተራ ቁጥር 5.1 ላይ የተዘረዘሩትን ጥቅሞች ማግኘቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሰጠውን መብት በአግባቡ ከመጠቀም እና ከባለስልጣኑ ጋር በትብብር መንፈስ ከመስራት አኳያ የሚኖርበትን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል። በመሆኑም የሚከተሉትን ኃላፊነቶችን የመወጣት ግዴታ ይኖርበታል፤

- በጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት የተሰጠውን ልዩ መብት አለአግባብ ያለመጠቀም፤
- የገቢም ሆነ ወጪ ዕቃዎች ለፍተሻ ሲመረጡ ተባባሪ መሆን፤
- በድርጅታቸው ውስጥ የስነ ምግባር ችግር ያለባቸው ሰራተኞች እንደ ጥፋቱ መጠን እርምጃ የመውሰድ፤

➢ ድርጅቱ ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሲመረጥ የኦዲት ሂደቱ በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆን አስፈላጊው ሰነዶች በማቅረብ የሚጠየቁ መረጃዎችን በመስጠት እንዲሁም ለሥራ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ተባበሪ መሆን፤
➢ በገቢ ግብር የሚፈለግባቸውን ክፍያ በወቅቱ የመክፈል፤
➢ ለባለስልጣኑ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ሲጠየቁ ተገቢውን መረጃ የመስጠት፤
➢ በባለስልጣኑ ኦዲተሮች የሚሰጡ የማስተካከያ ምክር መተግበር እና ተገቢውን የአሰራር መሻሻያ ማድረግ፤
➢ በድርጅቱ ውስጥ የሰራር እና የቦታ ለውጥ ወዘተ ሲደርግ በወቅቱ ለባለስልጣን መ/ቤቱ የማሣወቅ እና
➢ የሚገጥማቸው ችግር በየወቅቱ ሪፖርት ማድረግ እና ችግርችን በጋራ ለመፍታት ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

# 6. የአስፈፃሚ መ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

## 6.1.የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚሰጡ አስፈፃሚ መ/ቤቶች

የዕቅውቅና ሠርተፍኬት የሚሰጥ አስፈፃሚ መ/ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

1. የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል የዕውቅና ሠርተፍኬት ሊሰጣቸው የሚገቡ ልማታዊ ባለሀብቶችን ለመለየት እንዲቻል በዚህ ሠነድ ክፍል 3.2. ባለሀብቱ በተሠማራበት የሥራ ዘርፍ ተለይቶ በተዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት መሠረት የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚሰጠውን ባለሀብት የመለየት እና ለባለስልጣኑ በወቅቱ የማሳወቅ፣
2. የዕውቅና ሠርተፍኬት ለመስጠት በሚደረገው የማረጋገጥ ስራ ሂደት ውስጥ አመልካቹ በሠነድ የሚያቀርባቸውን ማስረጃዎች የተሟሉ መሆናቸውን እና ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የአመልካቹን ተቋም በአካል በመገኘት የመገምገም፣
3. በዚህ ሠነድ የአስፈፃሚ መ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ተብለው የተለዩ ሥራዎች ለማስፈጸም የሚያስችል የሥራ ክፍል ማደራጀት፣
4. የዕውቅና ሠርተፍኬት ለሚሰጣቸው ተጠቃሚዎች የሚኖራቸውን መብት እና ያለባቸውን ግዴታ በፅሁፍ የማሳወቅ፣እና
5. በተሰጣቸው የዕውቅና ሠርተፍኬት ሽፋን አለአግባብ የሚጠቀሙ ተጠቃሚዎች ላይ ከባለስልጣኑ በሚሰጥ መረጃ መሠረት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ፣

## 6.2.የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

1. የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት የሚያስገኝ የዕውቅና ሠርተፍኬት እንዲሰጣቸው ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ስማቸው በደብዳቤ ለተገለጹ ድርጅቶች አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ሠርተፊኬት የመስጠት፣
2. የዕውቅና ሠርተፍኬት የተሰጣቸውን ልማታዊ ባለሀብቶች መረጃ በአግባቡ መዝግቦ የመያዝ፣ ለሁሉም የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤቶች የማሳወቅ፣
3. የዕውቅና ሠርተፍኬት የተሰጣቸው በልዩ ሁኔታ የጉምሩክ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችላቸው በአውቶሜሽን ሲስተም የታገዘ አሠራር የመዘርጋት፣
4. በተሰጣቸው የተጠቃሚነት መብት ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ ይሄው የአገልግሎት አሰጣጥ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በአግባቡ መፈፀሙን መከታተልና ማረጋገጥ፣
5. ተጠቃሚዎች በተሰጣቸው መብት በአግባቡ እየተጠቀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግና ግኝቶችን በወቅቱ የዕውቅና ሠርተፍኬት ለሰጪው አስፃሚ መ/ቤት የማሳወቅ፣እና
6. በተሰጣቸው ልዩ መብት አጠቃቀም መልካም አፈፃፀም ያላቸውን በመለየት ይበልጥ ሊበረታቱ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ናቸው።

የምስክር ቁጥር............
Certificate No.........

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
# Ethiopian Revenue and Customs Autority

## ለጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት
## Customs special service authorization certificate

የድርጅት ስም ______________________________
Name of the Organization______________________

የተሰጠበት ቀን ____________
Issue Date ____________

የታክስ መለያ ቁጥር ________________
TIN No ____________

ድርጅቱ የተሰማራበት ዘርፍ ______________
Sector ____________________

ያፀደቀው..................................
Authorized by......................

ማህተም ......................
Seal ......................

☎ 0116-62-98-84 ✉ 2559

## የዕውቅና ሠርተፍኬት የሚያስገኘው ጠቀሜታ

1. በገዝትተኛ ሥጋት ደረጃ ተመድበው ፈጣን አገልግሎት የማግኘት፤
2. ከሰነድ ምርመራ እና ፍተሻ ጋር በተያያዘ እንደአስፈላጊነቱ የሚደረግ የጉምሩክ ቁጥጥር የቅድምያ አገልግሎት የማግኘት፤
3. የፍተሻ አገልግሎት በራሱ በተጠቃሚው መጋዝን የማግኘት፤
4. በዝቅተኛ የቅድመ ዕቃ አወጣጥ የጉምሩክ ቁጥጥር እና ጣልቃ ገብነት የመስተናገድ፤
5. ቅድመ ዕቃ አወጣጥ (Prearrival clearance) የጉምሩክ ስነስርዓት መፈፀም ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን፤
6. የሚያቀርቡት አቤቱታና ቅሬታ በቅድሚያ እንዲታይ የሚደረግበት ሁኔታ የማግኘት፤እና
7. ባቀረቡት ኢንቮይስ መሰረት እነዲስተናገዱ ማድረግ እና በቀጣይ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እንደ አስፈላጊነቱ የሚታይበት ሁኔታ፡፡

## ዕውቅና ሠርተፍኬት የተሰጠው የሚኖርበት ግዴታ

1. በጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት የተሰጠውን ልዩ መብት አለአግባብ ያለመጠቀም፤
2. የገቢም ሆነ ወጪ ዕቃዎች ለፍተሻ ሲመረጡ ተባባሪ መሆን፤
3. በድርጅታቸው ውስጥ የስነ ምግባር ችግር ያለባቸው ሰራተኞች እንደ ጥፋቱ መጠን እርምጃ የመውሰድ፤
4. ድርጅቱ ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሲመረጥ የኦዲት ሂደቱ በአግባቡ ተፈጻሚ እንዲሆን አስፈላጊው ሰነዶች በማቅረብ የሚጠየቁ መረጃዎችን በመስጠት እንዲሁም ምቹሁኔታ በመፍጠር ተባበሪ መሆን ፤
5. በገቢ ግብር የሚፈለግባቸውን ክፍያ በወቅቱ የመክፈል፤
6. ለባለስልጣኑ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ሲጠየቁ ተገቢውን መረጃ የመስጠት፤
7. በባለስልጣኑ ኦዲተሮች የሚሰጡ የማስተካከያ ምክር መተግበር እና የአሰራር መሻሻያ ማድረግ፤
8. በድርጅቱ ውስጥ የሰራር እና የቦታ ለውጥ ወዘተ ሲደርግ በወቅቱ ለባለስልጣን የማሣወቅ እና
9. የሚገጥማቸው ችግር በየወቅቱ ሪፖርት ማድረግ እና ችግርችን በጋራ ለመፍታት ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡